# የጥላቻ-ፖለቲካ ለኢትዮጵያ ህልውና ጠንቅ ነው

ከ ኣብርሃም ያየህ
ሓምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም. (August 6, 2008)

**ባሁኑ ጊዜ፣ በኢትዮጵያ የቃሚዊው ጎራ፣ የኣብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ነን ባይ ሃይሎችና ደጋፊዎቻቸው ዋነኛ የማታገያ ስልት ሆኖ በማገልገል ላይ ያለው በጥላቻ የተመሰረተ ፖለቲካ ነው፡፡ ይህ መርዘኛና ኣደገኛ የጥላቻ-ፖለቲካ፣ በትግራይ ስም በሚንቀሳቀሱ ሃይሎች ወይም በገዢው ፓርቲ ብቻ ያተኮረ ኣይደለም፡፡ አትኩሮቱ፣ በጅምላ ኣጠቃላዩን የትግራይ ህዝብ ዒላማ ያደረገ ነው፡፡ የህዝባቸውና ያገራቸው ህልውና የሚከነክናቸው ዜጎች፣ የዚህ ኣደገኛ በሽታ መዘዙ በትክክል ተረድተው ኣጥብቀው ካልታገሉት በቀር፣ ሄዶ-ሄዶ በመጨረሻ ኢትዮጵያን በመበተን ያለው ሚና እጅግ ወሳኝ ነው፡፡**

ጥላቻ ኣንድ ራሱ የቻለ ከባድ በሽታ ብቻ ሳይሆን፣ የብዙ በሽታዎች ምንጭ ጭምር ነው፡፡ ኣንድ ሰው ኣንዴ በዚህ በሽታ ከተለከፈ ደግሞ ከበሽታው በቀላሉ ለመፈወስ ቀላል ኣይደለም፡፡ ይህ ፀረ-ትግራይ ህዝብ የሆነ በጥላቻ የተመሰረተ የፖለቲካ በሽታ ጥልቀቱና ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ ከማመላከቴ በፊት፣ ጥላቻ የሚያስከትለውን ኣደገኛ ስቃይ የሚያሳይ ኣንድ ኣስገራሚ ገጠመኝ ኣንባቢዎቼን ለማጋራት እሻለሁ፡፡

ቦታው በምዕራብ ኬንያ ከፍታ ቦታዎች፣ በቢክቶርያ ሃይቅ ጠረፍ በምትገኘው "ኪሱሙ" የተባለች ውብ ከተማ ነው፡፡ በምስራቅ ኣፍሪካ በስደት በቆየሁበት ወቅት፣ በናይሮቢ ከተማ የተዋወቅሁዋቸው የኣንግሊካን ቤተ-ክርስትያን ቄስ (ፓሰተር) የሆኑ ኣንድ ደግ ወዳጅ ነበሩኝ፡፡ እኚሁ ወዳጄ፣ ኣንዲት በህመም የተጠቃች የመንፈስ ልጃቸው ለመጠየቅ ኣብሬያቸው ከናይሮቢ ወደ ኪሱሙ እንድከተላቸው ጋበዙኝና ኣብረን ሄድን፡፡ ኪሱሙ ከተማ እንደደረስንም ወደ ታማሚዋ መኖሪያ ቤት ኣመራን፡፡ የኬንያ ዜጋ የሆነችው ታማሚዋ እህታችን፣ ያንድ ትልቅ ፋብሪካ ባለቤት የሆነ እጅግ ባለፀጋ ሰው ሚስት ናት፡፡ ከሴትዮዋ ቤት እንደደረስን፣ ሴትዮዋ በፍፁም ደስታና ፍቅር ተቀብላ በእጅጉ አስተናገደችን፡፡

መስተንገዶው እንዳበቃ፣ ፓሰተሩ ወዳጄ ወደ መጣንበት ጉዳይ በመግባት፣ እህታችን ስለ ህመሟ ምንነት እንድታስረዳቸው ጠየቋት፡፡ እሷም የህመሟን ስሜት ኣንድ ባንድ ቆጥራ በዝርዝር ኣስረዳቻቸው፡፡

ፓስተሩ ከከፍተኛ መንፈሳዊ እውቀታቸው በተጨማሪ በስነ-ኣእምሮ ትምህርት በኣፍሪካና በእንግሊዝ ኣገር ከሚገኙ እውቅ ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ እውቀት የገበዩና የብዙ ዓመታት የስራ ልምድ ያካበቱ ኣባት ናቸው፡፡ ታማሚዋ እህታችን ከጠቀሰቻቸው የህመሟ ስሜቶች በመነሳት ሰፊ ትምህርት ከሰጡን በሁዋላ፣ ሴትዮዋ ከባሏ፣ ከጎረቤቶቿ፣ ከጓደኞቿ፣ ወዘተ. ያላትን ግንኙነት ምን እደሚመስል እንድትነግራቸው ጠየቋት፡፡ ታማሚዋም፣ ከሁሉም ጋር በፍፁም ሰላምና መግባባት ላይ የተመሰረተ ግኑኝነት እንዳላት ገለፀችላቸው፡፡ ነገርን ነገር እያነሳ፣ ብዙ ከተጨዋወትን በሁዋላ፣ ፓሰተሩ፣ ሰው ራሱን ሲጠላ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጥላቻ ሲያሳድር፣ ሴትዮዋ የዘረዘረቻቸውን የህመም ስሜቶች በሚመስል በሽታ ሊለከፍ እንደሚችል ገለፁላት፡፡

ፓስተሩ ገለፃቸውን እንዳበቁ፣ ሴትዮዋ ዓኖቿን ከፓስተሩ ዓይኖች ነቅላ፣ ኣንድ የዘነጋችው ነገር ያለ ወይም ኣንድ ኣስፈላጊ እቃ ጠፍቶባት የምትፈልግ ይመስል፣ በትካዜ ባህር ሰጥማ ኣንገቷን ወደመሬት ኣቀርቅራ ደርቃ ቀረች፡፡

ፓስተሩም፣ ኣንገቷን ወደ መሬት ኣቀርቅራ በትካዜ ባህር ውስጥ በመንሳፈፍ ላይ ወደነበረችው የመንፈስ ልጃቸው ጠጋ ብለው፣ በሁለት እጆቻቸው ሁለቱም እጆቿን ይዘው መፀለይ

ጀመሩ፡፡ "እግዚኣብሄር በደላችንን ይቅር የሚለን፣ እኛም የበደሉንን ይቅር ስንል ብቻ ነው" በሚል መርህ የተመረኮዘ ልብ የሚመስጥ ፀሎት ካሰሙ በሁዋላ፣ ሴትዮዋ የጠላችውን ወይም ያስቀየማትን ሰው ኣሁንኑ ከልቧ ይቅር እንድትል ኣዘዟት፡፡ ሴትዮዋ ግን ይብስኑ ስቅስቅ ብላ በማልቀስ ተንሰፈሰፈች፡፡

ኣንጀት በሚበላ ሆኔታ በለቅሶ የምታቃስተዋ እመቤት፣ ለቅሶዋን ኣቁማ እንድታዳምጣቸው ፓሰተሩ እንደገና ትእዛዝ ሰጡ፡፡ ቀጥለውም፣ "ለመሆኑ ኣንቺን ያስቀየመሽና የጠላሺው ሰው ማን ነው? ያስቀየመሽን ሰው ጠርተን ልናሰታርቃቸሁና ኣንቺም ይቅር እንድትይ፣ እሱም፣ በርግጥ በድሎሽ ከሆነ፣ ይቅርታ እንዲጠይቅሽ ለማድረግ እችላለን፡፡ ይህን ካደረግን ደግሞ፣ ከተጠናወተሽ በሽታ ተፈውሰሽ ይህንን በእግዚኣብሄር ፀጋ፣ በባለቤትሽ ትጋትና ጥረት የተገኘኸውን ሲሳይ በደስታ እያጣጣምሽ ቀጣዩ ህይወትሽን በሰላም መምራት ትችያለሽ" በሚል ታማሚዋን ኣስረዷት፡፡ ስትዮዋ ግን፣ ጭራሽ ብሶባት፣ ስቅስቅ ብላ በማልቀስ መሬት ላይ ወድቃ ስትንፈራገጥ፣ እኔንም ጭምር አስጨነቀቺኝ፡፡ ፓስተሩና እኔ እንደ ምንም ብለን ተደጋፍፈን ከወደቀችበት አንስተን ወደ በረንዳ ኣውጥተን ትንሽ ኣየር እንድትወስድ ኣድርገን ነፍሷን መለስነው፡፡ ሴትዮዋን የተጠናወተው የጥላቻ መንፈስ ምን ያህል ከባድ በሽታ እንደሆነ ለኔ ግልፅ የሆነልኝ ግን ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተውን ክስተት ስመለከት ነበር፡፡

የፓስተሩ ትእዛዝ የዋዛ ትእዛዝ ኣልነበረምና፣ ሴትዮዋ፣ ለንስሃ ኣይሉት ለኑዛዜ፣  ታሪኳን እንዲህ ስትል ዘረዘረች፡፡ "እውነት ነው፤ ኣንዲት ሴት ከልብ ጠላቻለሁ፡፡ እሷም የባለቤቴ እናት ናት፡፡ በኔ ላይ ያሳደረችው ጥላቻ እጅግ ፈታኝና ከባድ ስለሆነ እንዴት ኣድርጌ ይቅር እንደምላት ስለሚከብደኝ ነው የተጨነቅሁት፡፡ ለዚህ ሁሉ በሽታ የዳረገችኝ እሷ ስለሆነችም ነው የምጨነቀውና የማለቅሰው፡፡ ወዘተ…" ብላ ትረካዋን በማቋረጥ እንደገና በሲቃ መንሰቅሰቋን ቀጠለች፡፡

ደጉ ፓስተርም ቀጠሉና፤ "ለመሆኑ ኣማትሽ ምን ዓይነት በደል ብታደርሰብሽ ነው እንዲህ ያለ ስቃይ ውስጥ የገባሺው?" በማለት ጠየቋት፡፡

እህታችንም የደረሰባትን በደል እንዲህ ስትል ኣስረዳች፡፡ "እኔ ባለቤቴን ከመጠን ያለፈ እወደዋለሁ፡፡ እሱ ለኔ የማይሆነው ነገር የለምና፡፡ እሱም አኔን እንደ ሚስቱ ብቻ ሳይሆን እንደ ልጁ ጭምር ነው የሚወደኝ፡፡ እኔ ከምጨነቅ እሱ ቢጨነቅ፣ እኔ ከምታመም አሱ ቢታመም ይመርጣል፡፡ ታዲያ እንዲህ እየተፋቀርንና እየተሳሰብን በደስታ ስንኖር እግዚኣብሄር ስላልፈቀደልኝ ልጅ ኣልሰጠኝም፡፡ ከባለቤቴ ጋር ፍሬ ኣላፈራሁም፡፡ ባለቤቴ ግን፣ እኔን ከማግባቱ በፊት የወለዳቸው ሁለት ልጆች ኣሉት፡፡ እኔም የሱ ልጆች የኔም ልጆች ናቸው ብየ በፍፁም ህሊናየ በመቀበል ከልብ የመነጨ የእናትነት ፍቅር በመለገስ ልጆቻችን በደስታ እናሳድጋለን፡፡ ባለቤቴም ሆነ ልጆቹም በዚህ እጅግ ደስተኞች ናቸው፡፡ የባለቤቴ እናት ግን ልጇ፣ ባለቤቴን፣ ነጋ ጠባ በመወትወትና በመጨቅጨቅ፣ 'ይቺን መካን ላም ከምትቀልብ እሷን ፈትተህ ዘር የምታስቀርልህ ሌላ ሴት ኣግባ' እያለች ለዘመናት ስትጨቀጭቀው ኖራለች፡፡ ባለቤቴ ግን፣ ሃሳቧን በመቃወም ብቻ ሳይወሰን፣ ጭራሽኑ ከቤታችን እንዳትደርስ እስከ መከልከል ደርሷል፡፡ ወዘተ." በማለት ኣሁንም እንባዋን እያረገፈች ተናገረች፡፡

ፓስተሩም ቀጠሉና "ታዲያ ምን ኣለበት! ሰይጣን ኣሳስቷት ክፉ ተናገረች እንጂ፣ ባለቤትሽ እስካልወደደላትና ትዳርሽ እስከጠናልሽ ድረስ፣ ስለ ሴትዮዋ ምን ያስጨንቅሻል! እግዚኣብሄር ይህን የመሰለ ቅዱስ ባል ስለሰጠሽ፣ ፈጣሪሽን ብቻ ማመስገን ነው፡፡ ነገር ግን፣ እንዲህ ያለ የተባረከ የትዳር ጓደኛ ለሰጠሽ ቸር ኣምላክሽ ዋጋውን ኣልከፈልሺምና እጅግ ተሳስተሻል፡፡ ኣሁንም ጊዜው ኣላለፈምና ዋጋውን መክፈል ይገባሻል፡፡ ሰይጣን ሊያጠቃሽ በተፈታተነሽ ጊዜ ከጎንሽ ላልተለየው ኣምላክሽ ዋጋውን ለመክፈል ደግሞ፣ ብዙ ልፋትና ድካም የለብሽም፡፡ ይቺን ያስቀየመቺሽን ሴት በፍፁም ህሊናሽ ከልብሽ ይቅር በማለትና ለሷም በመፀለይ ብቻ እዳሽን መክፈል ትችያለሽ፡፡ ከዚህ የበለጠ የምትጠየቂው የእዳ ክፍያ የለም" በማለት እጅግ የሚመስጥ ኣባታዊና መንፈሳዊ ምክራቸውን ለገሷት፡፡ ቀጥለውም፣ "ለመሆኑ የባለቤትሽን እናት ኣግኝቸ ለማነጋገር፣ ለመምከርና ኣብሬያት ለመፀለይ ኣድራሻዋ ከወዴት ነው?" ሲሉ ጠየቁ፡፡

እህታችንም ስትመልስ፣ "ቅዱስ አባቴ፤ የባለቤቴን እናት ሊያገኟት አይችሉም፡፡ መጥፎ ሰው ስለሆነች፣ ሊያገኟት የማይችሉ መሆኑም በራሱ መልካም ነገር ነው፡፡ መጥፎ ሴት! - መጥፎ ሴት! - እጅግ መጥፎ ሴት ናትኮ! በማለት ሃይለ ቃል በተላበሰ መንፈስ ተናግራ በረጅሙ ተነፈሰች፡፡

መልካሙ ፓስተርም፣ "የት ብትሄድ ነው? ከአገር ውጭ ናት? ወይስ ያለችበት ስለማታውቁት ነው? በማለት ጥያቄያቸውን ወረወሩ፡፡

እህታችንም፣ በከፊል ተነቃቃችና፣ "አባቴ የለችም'ኮ! ሴትዮዋ ሞታለች፡፡ ከሞተች አሁን ሶስት ዓመታት አለፉት" በማለት ገለፀችላቸው፡፡ እኔም ይህንን ስሰማ፣ በጣም ገርሞኝ እንደ እንጨት ደርቄ ቀረሁ፡፡ እኔም በልቤ ውስጥ፣ አማትዋ የፈለገውን ያህል ብትበድላት፣ የሞተን ሰው እንዲህ መጥላት ምን ያስፈልጋል? ስል ራሴን በራሴ ጠየቅሁ፡፡ ከዚያ በሁዋላ ፓስተሩ፣ በህይወቴ ልረሳው የማልችል ትልቅ መልእክት ያዘለ ትምህርት ሰጥተውን፣ እኔም ያለቺኝን ትንሽ ምክር ወርውሬ፣ ሴትዮዋን አረጋግተን - ፈውሰን ማለት ይቻላል - ወደመጣንበት ተመለስን፡፡

እንግዲህ ይህ ገጠመኝ የሚያስተላልፈው መልእክት ቢኖር፣ አንድ ሰው በጥላቻ በሽታ ከተለከፈ፣ በህይወት ያለን ሰው ብቻ ሳይሆን በመቃብር ውስጥ ያለን ሰው ጭምር መጥላቱን እየቀጠለ ራሱንም በበሽታ እያሰቃየ የሚኖር መሆኑን ነው፡፡ ለኔ በግሌ፣ የዚች ምስኪን እህታችን እውነተኛ ታሪክ ከፍተኛ ትምህርት ሰጥቶኛል፡፡ ይህንን ገጠመኜን ተከትሎ ከጥቂት ዓመታት በሁዋላ ባንዲት ሰበበኛ ሬዲዮ አማካኝነት በተሰራጨ መርዘኛ የጥላቻ ፖለቲካ፣ በሩዋንዳ ህዝብ ላይ የደረሰውን እልቂት በቅርብ ተገኝቶ ስመለከት፣ እጅግ ቢያሳዝነኝም፣ ብዙ አላስገረመኝም፡፡ በዩጎዝላቪያ፣ በቅርቡም በሱዳን/ዳርፉር የሆነውንም እንደዚሁ አስለቀሰኝ እንጂ አላስደነቀኝም፡፡ የብተናውና የእልቂቱ ዋነኛ ሰበብ ጥላቻ የሚሉት በሽታ ለመሆኑ የኬንያዊቱ እህቴ ተመክሮ አስተምሮኛልና፡፡ ስለሆነም፣ ይህንን ታሪካዊ ገጠመኝ እያስታወስኩ፣ ባሁኑ ጊዜ ጥላቻ የሚባል በሽታ ባገራችን መሬት መስፈኑን በመገንዘብ፣ ከሁሉም በላይ የሚያሳስበኝ ነገር ቢኖር፣ ይህ በሽታ በህዝባችን ላይ መጥፎ አደጋ ያደርስ ይሆን? የሚል ስጋት ነው፡፡

ጥላቻ ምን ያህል መርዘኛ እንደሆነ ገጠመኜን ካጋራሁ ዘንዳ፣ ወደ ተነሳሁበት አርእስተ ነገር ላምራ፡፡

## የጥላቻ ፖለቲካ ተመክሮ በኢትዮጵያ

በአገራችን በኢትዮጵያ፣ በተለያዩ ጊዚያቶች የጥላቻ ፖለቲካ ተከስቶ ብዙ ጥፋት አስከትሏል፡፡ በረቂቅነቱና በአሳሳችነቱ ወደር ያልተገኘለት፣ አሁንም እንደ ትክክለኛ ታሪክ ተወስዶ እየቀጠለ ያለው ግን፣ የአፄ ምንሊክ ህጋዊ አልጋወራሽ በነበሩት በአቤቶ እያሱ ሚካኤል ላይ የተካሄደው የፖለቲካ ጥላቻ እጅግ አስገራሚ ነው፡፡ ወላጅ አባቴ፣ ልጅ ያየህ መልክ-ፄዴቅ፣ የአፄ ምንሊክ ታማኝ ባለሟል የነበሩት አንቱ ክቡር ደጃዝማች ገብረ-ስላሴ ባርያ-ጋብርን ተከትሎ ወደ አዲስ-አበባ ሄዶ ለአስር ዓመታት እዚያ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉ ከልጅ ኢያሱ ሚካኤል ጋር የቀረበ ግኑኝነት እንደነበረውና፣ ልጅ ኢያሱ ለኢትዮጵያ የነበራቸው የቅርብና የሩቅ ጊዜ ራእይና እቅድ (short and long term plan) ምን እንደነበር በዝርዝር ይነግረን ነበር፡፡ ስለሆነም፣ ታሪክ ፀሃፊዎች ነን ባዮች ስለ ልጅ ኢያሱ የፃፉትን ፍሬ-ከርስኪ ሁሉ እንደወረደ አይቀበለውም ነበር፡፡ የዚህ መጣጥፍ ትኩረት ባይሆንም፣ "**ፈረሴ፣ የምፅዋንና የጂቡቲን የጨው ውሃ ሳላስጠጣ ዘውድ አልጭንም**" የሚል ፅኑ አቋም የነበራቸው የምንሊክ ህጋዊ አልጋ-ወራሽ፣ አልጋቸውንና ህይወታቸውን ብቻ ሳይሆን መቃብራቸውም ጭምር ደብዛው ጠፍቶ የቀረው በውሸት በተመሰረተ የጥላቻ ፖለቲካ እንደሆነ፣ በሰነድ በማስደገፍ ጭምር፣ በሚገባ ማስረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከ-1960'ዎቹ ወዲህ በተካሄዱ የተለያዩ የፖለቲካ ትግሎች የጥላቻ ፖለቲካ ከፍተኛ የመቀስቀሻና የማወናበጃ መሳሪያ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባና ስም መጥራት ሳያስፈልገን፣ ከተማሪው ትግል ጀምሮ እስካሁን ድረስ እየተንቀሳቀሱ ያሉ የፖለቲካ ሃይሎች

ኣንዱ ሌላውን ለማሸነፍና ከህዝብ በመነጠል ደጋፊ ለማሳጣት የተጠቀሙት የቅስቀሳ ስልት በጥላቻና ስም በማጥፋት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በተለይ ደግሞ፣ የኤርትራ ድርጅቶችና በዚያድ ባሬ የተመራው የሶማሊያ መንግስት የጥላቻ ፖለቲካን በዋናነት የፕሮፓጋንዳና የመቀስቀሻ መሳሪያ ኣድርገው በመጠቀም ከራሳቸው ተርፈው ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ኣንቀሳቃሽ ሃይሎች ጭምር መጥፎ ኣብነት ኣውርሰዋል፡፡ የኤርትራ ፖለቲከኞች በትግራይ ህዝብና በኣማራው ህዝብ ላይ፣ የዚያድ ባሬ መንግስት በኣማራ ህዝብ ላይ ሲነዙት የነበረው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እጅግ ዘግናኝ ነበር፡፡ እነዚህ ሃይሎች፣ ለጊዜው ደጋፊ በማሰባሰብ ረገድ፣ የጥላቻው ስልት ኣገልግሏቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የጥላቻ ቅስቀሳዎቻቸው ውጤት ግን፣ "ስራ ለሰሪው - እሾህ ላጣሪው" እንዲሉ፣ ለራሳቸውም፣ ለዚያድ ባሬም ሆነ ለኤርትራ ድርጅቶች፣ ኣልበጀም ብቻ ሳይሆን ወድ ዋጋ ኣስከፈሏቸዋል፡፡ የዚያድ ባሬ ሶማሊያ የቅርጫ ስጋ እንደሆነች ቀጥላለች፡፡ ሻዕቢያም፣ ሲያቀብጠው ባድመን በወረረ ማግስት፣ ሆ ብለው የተነሱበትና የቀጠቀጡት የወያነ/ኢህኣዴግ ደጋፊዎችና ኣገር ወዳድ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ፣ "ከባድመ መልስ - ወደ መለስ" የሚል መፈክር ያነገቡ እልም ያሉ የወያነ/ኢህኣዴግ ጠላቶች በተለይም ኣማሮች ጭምር ነበሩ፡፡

የዚያድ ባሬን የጥላቻ ቅስቀሳ በሶማሎች ስነ ኣእምሮ ላይ ያስከተለው ኣሉታዊ ተፅእኖ በተመለከተ ኣንድ በዩጋንዳ የሚኖር ኣቶ ኢያሱ ሲራክ የተባለ ወዳጄ ያጫወተኝ ታሪክ በጣም ገላጭ ነው፡፡ ኣንዲት ሶማሊያዊት ሴት፣ ያቶ ኢያሱ ወዳጅ የሆነን ኣንድ የኤርትራ ተወላጅ፣ ኣማራ ምን እንደሚመስል እንዲያሳያት ትጠይቀዋለች፡፡ ኤርትራዊውም ይህንን ላቶ ኢያሱ ኣስረድቶ፣ ኣቶ ኢያሱን በናሙናነት ለማሳየት ሶማሊዋ ዘንድ ኣብሮት እንዲሄድ ይጋብዘውና ተስማምተው ይሄዳሉ፡፡

ኣቶ ኢያሱ፣ እጅግ የሚያምር መልክና ቁመና ያለው፣ በጣም የተማረና ያንድ ትልቅ የልብስ ስፌት ፋብሪካ ባለቤት የሆነ የኣማራ ብሄር ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወዳጄ ኣቶ እያሱ በኣለባበሱም ሆነ በሁለመናው ሺክ ያለ ሰው ስለሆነ፣ ኤርትራዊው ጓደኛው መልካም ናሙና መርጧል ማለት ይቻላል፡፡ ሶማሊዋ፣ መልከ-ቀናው ኣቶ ኢያሱን ኣይታ፣ ሰውየው ኣማራ ነው ብላ በመቀበል ራሰዋን ለማሳመን እንዴት እንደተቸገረችና እንደባከነች ኣቶ ኢያሱ ሲገልፀው እጅግ ያስገርማል፡፡ ባጭሩ ለመግለፅ ያህል፣ ኣቶ ኢያሱ፣ ያንን ዚያድ ባሬ የነገራት ዓይነት ኣማራ ነው ብላ ለመቀበል ኣእምሮዋ ኣልፈቀደላትም፡፡ በመጨረሻም፣ መልከ-መልካሙ ኣቶ ኢያሱ ሲራክ ሶማሊዋን ከሱ ጋር እንድትደንስ ይጠይቃትና፣ ኣማራነቱን ያመነችበት ባይሆንም - ድንገት የውነት ኣማራ ሊሆን ይችላል ከሚል ስጋት ይመስላል - ከኤርትራዊው ጋር እንጂ ከርሱ ጋር ለመደነስ ፈቃደኛ እንዳልሆነች ገልፃለት በዚሁ እንደተለያዩ ኣቶ ኢያሱ ኣጫውቶኛል፡፡ በኢትዮጵያችን ምድር ስለተገኘው የጥላቻ ፖለቲካ ተመክሮ ኣስመልክቸ ባጭሩ ይቺን ካልኩ ዘንዳ፣ ባሁኑ ወቅት ባገራችን ላይ ሰፍኖ የሚገኘው የጥላቻ-ፖለቲካስ ምን ይመስላል?

## በትግራይ ህዝብ ላይ ያተኮረው የጥላቻ ፖለቲካ በምን ይገለፃል?

ኣንዳንድ፣ የትርፍ ጊዜ ፖለቲከኞችና ኣክቲቪስቶች (Part-time politicians and activists)፣ ወዳጄ ታማኝ በየነን ጨምሮ፣ እኔና እንደኔ ያሉ የትግራይ ሰዎች የጥላቻ ፖለቲካን ኣምርረን የምንዋጋው፣ ኢህኣዴግ በህልውናችን ላይ ኣደጋ መኖሩን ሰብኮ ስላሳመነንና፣ ከዚሁ በመነሳት ስጋት ስላደረብን መሆኑን ባደባባይ ወጥተው ያለ ምንም ሃፍረት ይናገራሉ፡፡ እኔ፣ ይህንን ኣባባል የምወስደው እንደ ተራ ስድብና ንቀት ኣድርጌ ነው፡፡ ስለ ራሴ ብዙ ማውራት ባልፈልግም፣ ሓቁን ለመናገር ያህል፣ በበኩሌ ሙሉ ጊዜየን የማጠፋው በፖለቲካው ትግል እንጂ፣ እንደ ብዙዎቹ ኣብዛኛውን ጊዜየን ብር በማሳድድ የተረፈችዋን ትንሽ ጊዜ ደግሞ - እሷም ትንሽ ዝና እና ሳንቲም ለማትረፍ ሲባል - ፖለቲካ በማባረር ኣይደለም፡፡ ስለሆነም፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ መልክኣ-ምድር ስለሚካሄደው ማንኛውም ፖለቲካዊ ክንዋኔ፣ በማንኛውም መለኪያ፣ ወያነ/ኢህኣዴግ ስላስደነገጠኝ ብቻ ኣቋም የምወስድ ፍጥረት ልሆን ኣልችልም፡፡ በሌላ ኣነጋገር፣ በምርጫ 97 ሰሞን ከቅንጅት ጋር እንደ ኣሸዋ ትል ተፈልፍየ ብቅ ያልኩ ፍጥረት ስላይደለሁ፣ በጨዋታው ሜዳም ትንሽ የሰነባበትኩ ስለሆንኩ፣ ኣንድ የፖለቲካ ኣቋም ስወስድ በጥናት፣ በተጨባጭ መረጃና በሰከነ ግምገማ እንጂ፣ የኢህኣዴግ ፕሮፓጋንዳ ኣስደንግጦኝና ኣስደንብሮኝ ብድግ ብየ የምባዝን ፍጥረት ኣይደለሁም፡፡

የወያነም ሆነ የኢህኣዴግ ኣመራር፣ በራሱ ግኝት ወይም የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት ሲል የፈለገውን ሊል ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን፣ ወፍ-ዘራሽ ፖለቲከኞችና ኣሉባልተኞች እንደሚያስቡት፣ ኢህኣዴግ በገበያ ያቀረበልንን ሁሉ ዓይናችን ጨፍነን በመግዛት፣ ያንኑ ደግሞ መልሰን ለሌላ በላተኛ እናከፋፍላለን ማለት ኣይደለም፡፡ የኢህኣዴግ ፖለቲካ፣ በተለይም የኤርትራ ጉዳይ ኣያያዝ በተመለከተ፣ ወፍ-ዘራሽ ኣሉባልተኞቹ እንደሚያስቡት ዛሬ ሳይሆን፣ ከሃያ ዓመታት በፊት ነፍሳችንን ሸጠን የተቃወምንና ብዙ ዋጋ የከፈልን ሰዎች መሆናችን ታሪክ የዘገበው ሓቅ ስለሆነ፣ ባደባባይ ልንሰደብ ቀርቶ በድብቅ ልንታማም ኣይገባም፡፡ ስለ ራሴ ይህን ያህል ካልኩ የሚበቃ ይመስለኛል፡፡ "ኣውቆ የተደበቀን ቢጠሩት ኣይሰማም" እንጂ፣ የሰዳቢዎቻችንን ሸውራራ ኣመለካከት ለማረም መርዳት ይቻላል፡፡ ኢህኣዴግ ፈጥሮ የነገረን ሳይሆን፣ ባለፉት ኣስራ-ሰባት ዓመታት የሰበሰብናቸው፣ ራሳቸው የጥላቻ ፖለቲከኞቹ ምንም ሳያፍሩ በይፋ ባደባባይ የበተኗቸው ሰነዶችና በተለያዩ ሬዲዮ-ጣቢያዎቻቸው ያሰራጩዋቸውን እየመዘዝን በማቅረብ ሓቁን ለማስጨበጥ ኣይገደንም፡፡

እንግዲህ ወደ ቁምነገሩ እንመለስ፡፡ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚሰነዘረው የጥላቻ ቅስቀሳ ብቅ ያለው ገና ከጥዋቱ ማለትም ወያነ/ኢህኣዴግ ስልጣን በጨበጠ ማግስት ነበር፡፡ "**ትግራይ እስክትለማ ሌላው ሃገር ይድማ**" የሚል መሪ ቅስቀሳ በግላጭ በጋዜጣ ተፅፎ ያነበብነው፣ ኣሁን ብዙ የሚባልላቸው ጥቂት ተቋማት በትግራይ መሬት ሊመሰረቱ ቀርቶ፣ ኢህኣዴግ ገና ዳዴ በሚልበትና በመንበረ መንግስቱ ተደላድሎ ባልተቀመጠበት ወቅት ነበር፡፡ ይህንን መሪ ቅስቀሳ ተከትሎ ሌሎች ብዙ ቅስቀሳዎች በቡድን በተደራጀ መልኩም ሆነ፣ በተናጠል በግለሰቦች ኣማካኝነት እየተመራ፣ እንደ ደራሽ ጎርፍ ሲወርድ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ፣ ጭብጥ ለማያስያዝ ያህል፣ በተደራጀ መንገድና በተናጠል በትግራይ ህዝብ ላይ ሲረጩ ከነበሩ የጥላቻ ፖለቲከኞች ስራዎች መካከል ለናሙና ያህል ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

## በተደራጀ መልኩ የተሰራጨ የጥላቻ ፖለቲካ
## (ናሙና ቁጥር - 1)

ራሱን «የኢትዮጵያ አርበኞች ግምባር» (ኢአግ) በማለት የሚጠራው የፖለቲካ ድርጅት ሚያዝያ 30 ቀን 1986 ዓ.ም. ባፀደቀው **የድርጅቱ መርሀ-ግብር/ፕሮግራም** ላይ በማን-አለብኝነት ከረጨው ብዙ መርዝ ትንሽ ጠብታ ጨልፈን እንቅመስ። እጠቅሳለሁ፤

> «...ባለፉት መቶ ዓመታት ከአንድም ሦስት ጊዜ የኢትዮጵያን ህልውና ሊቀናቀን ከመጣ ጠላት ጋር በመሰለፍ የኢትዮጵያን ህዝብ የወጋ ኢትዮጵያ የሚለውንም ፅንሰ-ሃሳብ ያልተስማማውና ያልተዋጠለት ስለዚህም አገሪቱን በታትኖ ለማጥፋት ታጥቆ በተነሳው በትግሬው ጎሳ የሚካሄድ ትግል መሆኑ ከምንጊዜውም የበለጠ ዛሬ በግልፅ እየታየ በመምጣቱ፣
>
> «የኢትዮጵያ ህዝብ ወገኔ ያለውን የትግሬውን ጎሳ ከመሪው ለይቶ መብቱና ነፃነቱ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲጠበቅለት መታገሉ፣ ይሉኝታ መፍራቱ፣ አርቆ ማሰቡና፣ ራሱን አብልጦ አለመውደዱ እንደ አዋቂና ጀግንነት ከመቆጠሩ ይልቅ በቅሌታሙ ትግሬ ጎሳ ዘንድ እንደሞኝ፣ ደንቆሮና ፍራቻ ተደርጎ መወሰዱ፣ ትናንት በባንዳነት ከፋሽስቱ ጣሊያን ጦር ጋር ተሰልፎ ሲወጋን የነበረውን ወራዳ ታሪኩን ሸፍኖ የኢትዮጵያም ህዝብ እንደማያውቀውና እንደረሳው አድርጎ፣ ዛሬ ራሱን ጀግና አድርጎ የኢትዮጵያን ህዝብ ንቀት በተመላበት አንደበት ፈሪ ብሎ ሲጠራ እውነትም ውርደት ውስጥ የገባነው በዚህ ወቅት ነው ብንል ከእውነት የራቀ አነጋገር አይደለም።
>
> «በወያኔና በሻዕቢያ መሪነት በትግሬው ጎሳ አጋርነት ፋሽስቱ ጣልያን ሞክሮ በተሳነው የቅኝ አገዛዝ ይዘት ኢትዮጵያን የሚገዛውን ህገወጥ መንግሥት በኢትዮጵያ ስም ኢትዮጵያን በጎሳ በሃይማኖትና በክልል ከፋፍሎ ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ገጽታ ላይ ለማጥፋት የሚያደርገውን ሤራ አውድሞ የጠላቱን ጦርና ኢትዮጵያ የሚለውም ፅንሰሐሳብ ያልተስማማውን የትግሬውን ጎሳ ከኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ ለቆ እንዲወጣ የፖለቲካ ቅስቀሳና የመሣሪያ ጦርነት ማካሄድ።
>
> «ህገወጡን መንግሥትና የትግሬውን ጎሳ ከኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ ለማስወጣት በሚደረገው ትግል፣ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ፍጹም በሆነ መንገድ አምነው ከሚታገሉ ድርጅቶች ጋር ትብብር በማድረግ፣ ያልተባበሩትንም ማስተባበር፤

**«የኢአግን ዓላማዎች ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፣ ማንኛውም ከትግሬ ጎሳ ያልተዋለደና በጋብቻም ያልተዛመደ ኢትዮጵያዊ፣ እድሜው ከአስራ ስምንት (18) ዓመት በላይ የሆነ አባል ሊሆን ይችላል።**

**«በድርጅቱ ዓላማዎች የሚያምን ከትግሬ ጎሳ ያልተወለደ ማንኛውም ሰው በተባባሪ አባልነት መሳተፍ ይችላል።» የጥቅሱ መጨረሻ።**

እንግዲህ ይህን የመሰለ ልቅ የሆነና በጅምላ በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የፖለቲካ ጥላቻ እየተላለፈ ያለው ባንድ በተደራጀ የፖለቲካ ሃይል የመታገያ ፕሮግራም ውስጥ ተካቶ ነው፡፡ ይህ መርዛም የፖለቲካ ፕሮግራም ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፣ ድርጅቱ፣ ኢአግ፣ ጦርነቱን ያወጀው በትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ከትግራይ ተወላጅ ጋር በተጋቡ ሌሎች ሰዎች ጭምር መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ከትግራይ ተወላጆች ጋር የተጋቡና፣ በጅምላ በትግራይ ህዝብ ላይ የሚረጨውን የጥላቻ ፖለቲካ የተቃወሙ ኢትዮጵያዊያኖች የማግለል ጥቃት ሲፈፀምባቸው ኣይተናል፡፡

የዚህ ዓይነት እርኩስ የጥላቻ ፖለቲካ ኣገር ኣፍራሽ በመሆኑ፣ የሚጎዳው በተናጠል የትግራይ ህዝብ ሳይሆን ባጠቃላይ ኣገራችን ኢትዮጵያን ነው፡፡ እስካሁን ድረስም ቢሆን፣ ኣገር ወዳድ ዜጎች ከፍተኛ ትኩረት ስጥተው ስላልታገሉት፣ በብዙ ረገድ በውድ ኣገራችን በኢትዮጵያና በምስኪኑ ህዝባችን ላይ የማይናቅ ጉዳት ኣድርሷል፡፡ ስለሆነም፣ የትግራይ ህዝብ ልጆች ይህንን የመሰለ ኣገር በታኝ የሆነ የፖለቲካ ጥላቻ ጠንክረን የምንዋጋው ለትግራይ ህዝብና ለራሳችን በመቆርቆር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታችን የጋራችን ለሆነችው ኣገራችን ኢትዮጵያ ህልውና ስንል መሆኑን በትክክል ሊሰመርበት ይገባል፡፡

እኛ የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊያኖች የዚህ ዓይነቱ ፖለቲካ መዋጋት የጀመርነው ዛሬ "ለራስ ሲቆርሱ ኣያሳንሱ" ብለን ሳይሆን፣ ትናንት፣ የራሳችን ወንድሞች የሆኑ እነ ኢያሱ በርሀ/በርሄ፣ በህወሓት የኪነት ቡድን ውስጥ ተሸጉጠው፣ ኤርትራንና ሻዕቢያን እያወደሱ ኣማራን ሲሰድቡም ኣምርረን ተዋግተናቸዋል፡፡ ይህንን ያደረግነው ከነ ኢያሱ ጋር የግል ቁርሾ ኖሮን፣ ወይም ደግሞ ኣማሮች ተዋጉልን ብለውን ሳይሆን፣ ድርጊቱ ጥላቻን የሚሰብክና በዘለቄታውም ኣገር በታኝና ኣክሳሪ ፖለቲካ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡

## በተደራጀ መልኩ የተሰራጨ የጥላቻ ፖለቲካ

(**ናሙና ቁጥር** - 2)

ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበው ናሙና ደግሞ፣ ባሜሪካ ርእሰ-ከተማ በዋሺንግተን ዲ.ሲ. የመሸገውና፣ "ኢትዮጵያዊነት" ተብሎ በሚታወቀው ሬዲዮ ጣቢያ፣ በኢትዮጵያ ዘመን ኣቆጣጠር፣ ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም. (June 24, 2008) ያሰራጨው የሚለንየሙ-ዓመት ታላቁ ኣሰቃቂ የጥላቻ-ፖለቲካ ነው፡፡ የዚህ ሬዲዮ-ጣቢያ መሪና ኣስተባባሪ "ጓድ" ምርጫው ስንሻው በመባል የሚታወቅ፣ በደርጉ ዘመን በጎንደር ከተማ እልፍ-ኣእላፍ ወጣቶች የፈጀው የመላኩ ተፈራ ዋና ተባባሪ ካድሬና የኢሰፓ ሙሉ ኣባል የነበረ ነው፡፡ ኣሁን ደግሞ የሃይሉ ሻውል ቡድን ኣንጋፋ ተባባሪና የፕሮፓጋንዳ ኣቀናባሪ በመሆን ከፍ ያለ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ለባከነው የሃይሉ ሻውል ቡድን ደጋፊ ለማስገኘት እጅግ ኣበክሮ የሚሰራ ጭልፊት ነው፡፡ ስለዚህ ሬዲዮ ኣመሰራረትና፣ ስለ ኣስተናባሪው ስለ ምርጫው ስንሻው ሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ፡፡ ላሁኑ ግን ከላይ በተመለከተው ቀን በሬዲዮ የተሰራጨውና እኔ ቃል-በቃል ወደ ፅሑፍ የመለስኩትን ኣሰቃቂ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እንመልከት፡፡ (እጠቅሳለሁ)

**"ስለ ወልቃይት፣ ስለ ጠገዴ በርካታ በደሎች በኢትዮጵያ ተፈፅሟል፡፡ ያንን በደል በሚመለከት ከዚህ በፊት ያቀረብኩላችሁ የሚታወስ ነው፡፡ ሌሎችም ኣሳዛኝ የሆኑ መረጃዎች በየጊዜው ይደርሱኛል፡፡ ታዲያ፣ ዛሬም ጥቃቱ ቀጥሏልና፣ ዝም ማለቱም ኣግባብ ኣይደለምና፣ ጥቂት ስለ ደረሰኝ ነገር ላካፍላችሁ፡፡**

**"ወያነ ሓርነት ትግራይ ወልቃይትን እንደተቆጣጠረ፣ 3881 የወልቃይት ተወላጆችን ኣፍሶ ወደ ትግራይ ይወስዳል፡፡ እነዚሁ በሙሉ ወደዚሁ የሄዱት፣ 3881'ንዱ በሙሉ፣ ወልቃይት ውሰጥ የተያዘ በመሆኑ፣ ልጆቹስ እነዚያን የመሰሉ ወንዶች፣ እነዚያን የመሰሉ ቀላቢዎቼ የት ሄዱ? ብሎ ለመጠየቅ ኣልቻለም፡፡ በርግጥ እንደተያዘ ነው፡፡ የነዚህ ሰዎች ድራሽ ጠፋ፡፡ ደብዛቸው ጠፍቶ ቀረ፡፡ በኤርትራ 4000 ኢትዮጵያዊያን እንደዚሁ**

**በምርኮ ከተያዙ በሁዋላ ኣራት ሺ'ውም በመደዳ ተረሸነው ኣሸዋ ላይ መቅረታቸው የሚታወስ ነው፡፡ የነዚህም ቢሆን የቀረው ቁጥር በኣስር የሚቆጠር ነው፡፡ ለ4000 የተጠጉ ወልቃይቶች ትግራይ ተጭነው እንደሄዱ ታረዱ፡፡ ሁሉም ጭዳ ሆነው ቀሩ፡፡**

**"በዚህ ኣላበቃም፡፡ ከ 1991 እስከ 1994 ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ 279 ወጣቶችም፣ ሁሉም ወንዶች፣ እንደገና በኣሰሳ ታፈኑ፡፡ እነዚህም ደግሞ ወደ ትግራይ ተጫኑ፡፡ እናም ታረዱ፡፡ ኣልተመለሱም፡፡ ከዚህ በሁዋላ የወልቃይት መሬት ባል-ኣልባ ሴቶችን ኣቅፋ ቀረች፡፡ በርካታ ህፃናትም ኣባት-ኣልባ ሆነው እንዲኖሩ ለግፍ ተጋለጡ፡፡ እነዚሁ ሴቶችም ናቸው ለወደፊቱ የነ ኣረጋዊ በርሄ ሪፈረንደም[1] ድምፅ የሚሰጥ ዲቃላ እንዲፈለፍሉ የምርጥ ዘር ኮርማ ተመድቦላቸው በየቀኑ እየተገደዱ እስኪያረግዙ ድረስ የሚደፈሩት፡፡ እስኪያረግዙ ቀናቸው እየተጠበቀ የወር ኣበባቸው መምጫና መሄጃ እየተመዘገበ ክትትል ይደረግባቸዋል - ወያነ ባቋቋመው ጤና ጣቢያ፡፡**

**"እነዚህ ሰቶችም ወለዱ፡፡ ያልፈለጉትም ዲቃላ እንዲያሳድጉ ተገደው ኣሳደጉ፡፡ ስለሆነም፣ ዛሬ ወልቃይት ውስጥ ዘመድ ያለው ሁሉ -ልብ በሉ - የእህቴ ልጅ እንጂ፣ የወንድሜ ልጅ የሚል ከቶውንም ኣይገኝም፡፡**

**"የወያነ ጦር ወልቃይትን ከተቆጣጠረበት ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ፣ በመላው ሀገሪቱ በተለይ በወልቃይቶች ላይ የሚፈፀመውን በደል ስራየ ብሎ ለዘገበው ብዙ ትልልቅ የታሪክ መድበሎች ይወጡታል፡፡ ለናሙና ያክል ግን፣ ከዚህ ዘእይንተረፍ የወያነ ወንጀል ኣንድ ላክልላችሁ፡፡**

**"ወቅቱ ጥቅምት 1993 ዓ.ም. ነበር፡፡ ከ 25 የማይበልጡ የወያነ ወታደሮች ወደ ኣንድ መንደር ጎራ ይላሉ፡፡ መንደሩ ጭር ብሏል፡፡ ለወሬ ነጋሪ ወንድ በሰፈሩ ኣልነበረም፡፡ ከትንንሽ ህፃናት በቀር፡፡ ሁሉም በነቂስ ተለቅመው፣ ወዲያው እንደተለመደው ወደ ትግራይ ተጫኑ፡፡**

**"ወታደሮቹ ይህንን ሆኔታ ካጠናቀቁ በሁዋላ፣ ዘና ብለው፣ በየቤቱ ተሰማሩ፡፡ ወልቃይት ወንድ ኣልባ ሆናለች፡፡ እንኳን ጠመንጃ ሽመል የሚይዝ ወንድ የለም፡፡ እናም ባል-ኣልቦ ሴቶችና ኣባት-ኣልቦ ህፃናትም፣ ፍርሃትና ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት፣ የእለቱን እንግዶች ሆኔታ ዓይናቸው ፈዞ ይታዘባሉ፡፡ በሆኔታቸው ያልተደሰቱት ወታደሮችም፣ ያው ጉልበታቸው ኣፈሙዝ ነውና፣ ኣፈሙዝ ደግነው የሚፈልጉትን እንዲፈፁሙላቸው ያዛሉ፡፡ ሽብ-ረብ ብሎ ትእዛዙን የተቀበለ ግን ያን ቀን ኣልነበረም፡፡ ይህም ይበልጥ ብስጭትን ወለደና የሃይል እርምጃን ኣስከትሎ እነዚሁን ባል-ኣልባ ሴቶች በሰደፍ በኣፈሙዝና በእርግጫ መደብደቡን ተያያዙት፡፡**

**"ጭካኔ በተመላበት ሆኔታ ነበርና፣ ይህን ጭካኔ የተመለከቱት ህፃናት በሙሉ ዋይታቸውን ቀጠሉ፡፡ በለቅሶኣቸው ያልተደሰቱ ወታደሮችም እንደ እናቶቻቸው ህፃናቱንም በሰደፍና በኣፈሙዝ እያዳፉ ፀጥ ኣሰኟቸው፡፡ ኣመሻሹ ላይም ከስምሪት የተመለሱት በጎችና ፍየሎች ወደ ጋጥ ከመግባታቸው በፊት፣ የግፉ ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ፣ ቀን ፈርዶባቸው ሁሉም ወደ እርድ ኣመሩ፡፡ የተዘረፈው ኣባት፣ ወንድም፣ የተዘረፈችው እናት፣ እህት ብቻ ኣይደለም፡፡ የተጋዘው እንስሳውም ጭምር ነው፡፡**

**"ያች እለት ለዚያች መንደር የመስክ ቀን ሆና ዋለችና ኣደረች፡፡ እንዳይመሽ የለምና ብርሃንም ለጨለማ ቦታውን እየለቀቀ ሄደ፡፡ የምርጡ ዘር ኮርማዎች ዓይኖቻቸው ባረፉባቸው ሴቶች ላይ ኣስገድዶ የመድፈር ወንጀል ሲፈፅሙባቸው ኣደሩ፡፡**

**"የወንዶቹ ኣገር በፀጥታና በጨለማ ተወርሶ ብዙ የወርቆቹን ዲቃላዎች ሲያፀንስ ኣደረ፡፡ በምርጡ ዘር ወታደሮች ኣማካኝነት፡፡ ውርደት ማርኮ ያስቀመጣቸው ሴቶችም፣ ውርደቱ በነሱ ፈቃደኝነት የተፈፀመ ይመስል፣ ባልፈፀሙት ሓጢያት ኣፍረው ኣንደኛዋ የሌላኛዋን ፊት ላለማየት ሁሉም እንደ ባሕታዊ ራሳቸውን በየቤታቸው ለጊዜው ዘግተው ዋሉ፡፡ ወዲያውኑ ኣልቻሉም፡፡ ያንኑ እለት ማታውኑ ግን ብዙዎቹ ኣገር ጥለው ተሰደዱ፡፡ ግማሾቹም ሲቃ እየተናነቃቸው ኮሶና እንዶድ ሲጋቱ ሰነበቱ፡፡ ኣዎ! ዘግናኝ ቀናት ነበሩ፡ የሚቆጠሩት፡፡**

**"በዚህ መልክ ሁለት ወር ብሎም ዘጠኝ ወር ተቆጠረ፡፡ የምጥ ቀን ደረሰ፡፡ የጀግና ሚስትም የደመኛዋን ዲቃላ ኣምጣ ለመውለድ ዳግም ተምበረከከች፡፡እንደ የወርቅ-ውሃ ዓይነቶቹ ግን የባላቸውን ገዳይ፣ ባላቸውን ባፍ-ጢሙ ገድሎ መጥቶ ያፀነሰን ባል፣ ዲቃላ ኣምጦ ከመውለድ ሞትን መርጠው ገድለው ሞቱ፡፡ ኣንዳንዶቹም፣ ኣቅም እንኳ ባጣ**

---

[1] ኣረጋዊ በርሀ/በርሄ ስለ ውልቃይት የወደፊት እጣ-ፈንታ (ህወሓት ከስልጣን ሲባረር ማለት ነው) ምን እንደሚሆን ባንድ ጋዜጣ ተጠይቆ፣ ኣረጋዊ በሰጠው መልስ፣ የወልቃይት ጉዳይ "በሪፈረነደም (በህዝበ-ውሳኔ) ይወሰናል" ያለውን ነው ይህ የጥላቻ-ፕሮፓጋንዲሰት እየጠቀሰ ያለው፡፡

በሱ ላይ፣ በዲቃላው፣ መጨከን ኣያቅተኝም ብለው ህፃኑን ከእንግዴ-ልጁ ጋር ጠቅለለው በመቅበር ቁጭታቸውን ተወጡ፡፡ እናት የማትጨክነውን ጭካኔ ጨከኑ፡፡

"ሆኖም ይህ ድርጊት ወደ ባለ-ቀኖቹ ጆሮ ደረሰና በዙዎቹ እንደ ባሎቻቸው፣ እንዳባቶቻቸው እየታደኑ ባራስ-ቤታቸው እንዳሉ በነፍስ ማጥፋት መንጀል ተከሰው ወደ ትግራይ ተወሰዱ ተባለ፡፡ እንደ ባላቸው፣ እንደ ኣባታቸውም ሁሉ እነሆ ኣልተመለሱም፡፡

"የነዚህ ግፉኣን ልጆችም፣ ወንዶቹ ያባቶቻቸው እጣ-ፋንታ ሲወርሱ፣ ሴቶችም ዕድሜ ለወያነ እንደ ቀሪዎቹ የወልቃይት ሴቶች የምርጡ ዘር ኮርማ ቅምጦች ሆነዋል፡፡

"የወልቃይት መሬት ይህንና ይህን መሰል ብዙ እጅግ ገጠመኝ ታሪኮችን ኣቅፋ እነሆ የጎበዝ ያለህ ትላለች፡፡ ዛሬም ታምጣለች፡፡ እናም ቀንን ቀን እየቆጠረው ሲሄድ የነ ኣቶ ኣረጋዊ ሪፈረንደም ለዚህ ይመች ይሆናልና ባሻቸው ጊዜ ቢያደርጉት ምቹ ነው፡፡ (የጥቅሱ መጨረሻ)

ይህንን፣ እንኳን በራሳችን ወገን ላይ ቀርቶ በባእድ ላይ ተፈፅሟል ተብሎ ቢነገር እንኳ፣ ለመስማት የሚዘገንነው የ"ጓድ" ምርጫው ስንሻው ኣጥፊ ቅስቀሳ እንዳበቃ፣ ጣቢያው ለኣድማጮች ኣስተያየት ክፍት ተደርጎ ተለቀ ነበር፡፡ እናም ይህንን ዘግናኝ ዜና ከተከታተሉ ኣድማጮች ውስጥ እድሉን ኣግኝተው በከፍተኛ ቁጭትና ብስጭት ኣስተያየታቸውን ከሰጡት መሃል የጥቂቶቹን እነሆ፡፡ (እጠቅሳለሁ)

1ኛ-ኣድማጭ፤ "የዛሬውንና የበቀደምለቱን፣ የዓርብ'ለቱን፣ ያነበብከውን በድረ-ገፅ (website) ላይ ፖስት (post) ብታደርገው እናትመው (print እናደርገው) ነበር፡፡ ማድረግ ትችላለህ?

ምርጫው ስንሻው፤ ኣዎ ኣደርገዋለሁ የኔ ጌታ! እግዜር ይስጥልኝ፡፡

2ኛ-ኣድማጭ፤ እነዚህ ኣሁን የምታነባቸው፣ ወንድሜ እንዳለው፣ ፖስት (post) ኣድርገው፡፡ እኛ ይህን ሁሉ ኣናውቅም፡፡እና ይህንን ለጥፈው! - ለጥፈው እስኪ! ሁሉም ሰው ያንብበው፡፡ እንደገና ደግሞ፣ ይህ ጥሩ የጋዜጠኝነት ሙያ ነው፡፡ ራሱ ጋዜጠኛ ማለት ማጋለጥ ነው፡፡ ከዚያ በሁዋላ ህዝቡ ራሱ ኣክሽን/action (እርምጃ) ይወሳዳል፡፡ OK? እናም ይህ ጥሩ ስራ ነው፡፡ እናመሰግናለን፡፡

ምርጫው፤ እግዜር ይስጥልኝ - የኔ ጌታ!

3ኛ-ኣድማጭ፤ እሺ፣ ጋሼ ምርጫው፡፡ እና ይኸው! ስለ ተቃጥልሁ ነው - እኔ በዚህ ጉዳይ! በወልቃይት ጉዳይ፡፡ እኔ እንጃ! ያልሰማነውና በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ ህሊናችንን እየነካን ነው ያለው'ኮ! ምነው ጎንደር እንዲህ ዝም ኣለ? እኛ ኣናውቅም፡፡ እኔ ራሴ ኣማራ ነኝ፡፡ ኣላውቅም፡፡ ለምን እንዲህ እየተደረገ ለምን፣ ፍርድ ቤት እንኳ የለም፣ ለዓለም እንኳ ኣንጮህም፡፡ እና ኣንድ ነገር ኣናደርግም፡፡ እንግዲህ ይህ ከተፈጠረ ለምን ኣናልቅም? ምንን...እኔ ኣብጃለሁ በቃ! ታምሜኣለሁ በቃ! ይህ ነገር መፍትሄ ይፈለግለት፤ ኣዋቂዎችን ኣማክሩ፡፡እኛ እንኳን ኣማራ እ...ለምን እኔ ካሁን ወዲያ ስለ ኢትዮጵያ መጫወት ኣልፈልግም፡፡ በቃ! ስለ ኣማራነቴ ብቻ ነው የማውቀው፡፡ በቃ! ካሁን በሁዋላ፡፡

ምርጫው፤ ኣመሰግናለሁ የኔ ጌታ!

4ኛ-ኣድማጭ፤ ኣረ እኔ በጣም እ...ይህ'ኮ ለ-Human Right (ለሰብኣዊ መብት ተከራካሪ) መቅረብ የሚገባው ነው'ኮ! በጣም ነው የደነቀኝ! እኛ ይህንን'ኮ ኣናውቅም፡፡ ኣሁን የሱዳን ድንበር እንደተባለው ሁሉ ይኸም ተጠንቶ ግማሽ እውነት፣ ቅንጣት እንኳ ቢኖረው ዓለም ኣቀፍ ወንጀል ነው፡፡ ይኸ በሬዲዮ ብቻ ተነግሮ የሚቀር ሳይሆን ይህንን ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ ይህንን ዓይነት ክስ ኣለ፡፡ እንዲያው ለምንድን ነው? የኛ ሰው ካሜራ ይዞ ሰርግ ብቻ ነው የሚቀርፀው፡፡ ሰው ሲደበደብ፣ ሰው ሲታሰር ኣይቀርፅም፡፡ እና እኔ ግርም የሚለኝ ይህንን ያክል ወንጀል በኛው ላይ ሲፈፀም፣ እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የምሰማው፣ ለምንድን ነው ለኣምነስቲ ኢንተርናሺናል (Amnesty International) ለ- Human Right Watch፣ ለተባበሩት መንግስታት የማይተላለፈው? እነሱ ያጠኑታል - እባክህን - እባክህን የኔ ጌታ!

ምርጫው፤ የተከበሩ ወንድሜ! ትልቁ ችግራችን'ኮ ተቃዋሚው በሙሉ በወያነ infiltrate ተደርጓል (በወያኔ ሰርጎ-ገቦች ተወሯል)፡፡እንኳን ሌላ ቀርቶ .... (4-ኛ ኣድማጭ ምርጫውን ያቋርጡትና በንዴት ይቀጥላሉ)

4-ኛ ኣድማጭ በመቀጠል፤ እኔ፣ በነገራችን ላይ፣ ነገሩ ግን፣ እውነት እንዳንተ ዓይነት ጥቂት ጭላንጭል ነው ያለው ማለት ይቻላል፡፡ እና እባክህን የማንኛውም

**ብለህ ወይ ለዚህ ለሱዳን ድንበር ኮሚቴ ወይም ደግሞ እንደዚህ ዓይነት ኮሚቴ ተቋቁሞ ይህ ለ-human right (ሰብአዊ መብት ተከላካይ) ይቅረብ፡፡ ይህ'ኮ መለስን እንደ ሂትለር - አዶልፍ ሂትለር' - የሚያስጠይቀው'ኮ ነው፡፡ ይህ'ኮ impossible (የማይቻል/የማታይሰብ)....**

**ምርጫው፤ ይቅርታ አድማጭ፤ ሰዓቴ ስላለቀ ነው፡፡ በነገው እለት በስፋት እንወያያለን፡፡ ሰላም ሁኑ የተከበራችሁ አድማጮቼ፡፡ (የጥቅሱ መጨረሻ)**

***ማስታወሻ፤ ይህንን ከላይ የጠቀስኩት ጉድ በድምፅ ለመስማት ከፈለጉ እዚህ ድረ-ገፅ*** http://wmet1160.com/audio/winet/rss.xml ***ገብተው*** June 24'***ን መርጠው ማለትም በ*** Winet 2008.06.24 1700.mp3 ***ከሚለው ላይ ተጭነው ለማዳመጥ ይችላሉ፡፡***

*እንግዲህ እንደኔ ላለ ዜጋ፣ ይህንን እጅግ ዘግናኝ የሆነ ዜና ሰምቶ ተኝቶ ያድራል ብየ ለማመን እቸገራለሁ፡፡ ይህም ማለት፣ ይህንን የመሰለ ወንጀል በትክክል የተፈፀመ ለመሆኑ የ"ኢትዮጵያዊነት" ሬዲዮ ጣቢያ በቂ ማስረጃ የሚያቀርብልን ከሆነ፣ ይዋል ይደር ሳይባል ወንጀሉን ፈፀሙ በሚባሉት ሰዎች ላይ ወይም በገዢው ፓርቲ ላይ እንደ አንድ ሰው ሆነን መነሳት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ የፈለገው የፖለቲካ አመለካከትና የአቋም ልዩነት ቢኖረን እንኳ፣ በንፁህ ዜጎቻችን ላይ ይህን የመሰለ ዘግናኝና ኢሰብአዊ ወንጀል ተፈፀሟል ተብሎ ባደባባይ በሬዲዮ ተነግሮን ችላ የምንል ከሆነ፣ በበኩሌ ኢትዮጵያ የምትባል አገር - ሰው የሚባል ነገር የላትም፣ ብየ ለማጠቃለል እገደዳለሁ፡፡*

*ሌሎች በመንግስት ተፈፀሙ ከሚባሉ ድርጊቶች ይህንን ተፈፀመ የሚባለው ወንጀል ልዩ የሚያደርገው ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ መልሱም ቀላል ነው፡፡ ባጭሩ አንድ አብነት ጠቅሸ ራሱን "ኢትዮጵያዊነት" ብሎ የሚጠራው የሬዲዮ ጣቢያ ካቀረበልን "ዘር የማጥፋት ወንጀል" ጋር በማነፃፀር ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡*

*ለምሳሌ ያህል፣ ምርጫውን ተከትሎ የተገደሉት ዜጎቻችን ጉዳይ እንመልከት፡፡ መንግስት ከሚገባው በላይ ሃይል ተጠቅሟል? አልተጠቀመም? የሚለውን ለታሪክ ፍርድ ትተን፣ ድርጊቱ ሁላችንም ያሳዘነን ቢሆንም ቅሉ፣ መንግስት እርምጃወን የወሰደው በመንግስትነቱ ፀጥታ ለማስከበርና ተቃዋሚ ነን ባዮች ራሳቸውንና ልጆቻቸውን ሳያሳትፉ የቀሰቀሱት አላስፈላጊና የማይሰራ ረብሻ ለማስቆም ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ እንኳንና በአፍሪካ ምድር ቀርቶ፣ ባሜሪካና ባውሮጳም ቢሆን፣ የስድስት ወይም የሰባት ፖሊሶችን ህይወት የቀጠፈና በብዙ ሚልዮን ብር በሚገመት የህዝብ ንብረት ላይ እሳት የለኮሰ ረብሻ፣ በምንም ሚዛን አንድ መንግስት እንደ ተራ ረብሻ ቆጥሮ እርምጃ ከመውሰድ ይታቀባል ብሎ መጠበቅ የማይቻል ነው፡፡ ስለሆነም ተጠያቂነቱ በመንግስት ትክሻ ብቻ የሚያርፍ ሳይሆን በተቃዋሚው ሃይል መሪዎችና ረብሻውን በስውር በቀሰቀሱት ቡድኖች ጭምር ነው ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡*

*ይህ በ"ኢትዮጵያዊነት" ሬዲዮ የቀረበልን ወንጀል ግን፣ በባህሪውና በድርጊቱ ፍፁም የተለየና ለወንጀሉ መፈፀም ምንም ዓይነት ሰበብና ምክንያት ሊቀርብለት የማይችል የለየለት "ዘር የማጥፋት" ወንጀል ነው፡፡ በደል ተፈፀመባቸው የተባሉት ሰዎች የወልቃይት ተወላጆች በመሆናቸው ብቻ፣ "በወያኔ እና የትግራይ ተወላጆች በሆኑ ወታደሮች ብቻ" የተፈፀመ ደረቅ "ዘር የማጥፋት" ወንጀል ነው፡፡ ስለሆነም፣ ሌሎች ልዩነታችን እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህንን አገርና ህዝብ በመበተን ከፍተኛ ሚና ያለው ክስ በጋራ ልንቋቋመውና እውነት የተባለው 'ዘር የማጥፋትና የማፅዳት" ወንጀል የተፈፀመባቸው ንፁሃን ዜጎቻችን ካሉ፣ ፍትህ የሚያገኙበትና ወንጀለኞቹም በዓለም ፍርድ ቤት ጭምር ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ የሁሉም አገርና ህዝብ ወዳድ ዜጋ ግዴታ ነው፡፡*

*በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህ ተፈፀመ የተባለው "ዘር የማጥፋት" ወንጀል በትክክል ለመፈፀሙ ከሳሹ የ"ኢትዮጵያዊነት" ሬዲዮ በቂ ማስረጃ ሊያቀርብ የማይችል ከሆነ፣ በሬዲዮ ጣቢያውና በምርጫው ስንሻው መንግስትና የትግራይ ህዝብ ክስ መስርተው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ መንግስት ከምንም በላይ ቅድሚያ መስጠት ያለበት የህዝብን ህልውና ማስከበር ስለሆነ ይህንን ድርጊት አቅልሎ ማየት የለበትም፡፡ ሆኖም ይህ የመንግስትና*

የትግራይ ህዝብ ግዴታ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ሃላፊነት ጭምር መሆኑ በትክክል በሚገባ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ "ከሞኝ በራፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንዲሉ ኢህአዴግን ለመታገል አማራጭ ያጡ የሰው ተባዮች፣ ይህን የመሰለ ዘግናኝና አስፈሪ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ደጋፊ በማሰባሰብ ፖለቲካ ለመሸጥና ብር ለማግበስበስ ሲሉ በቤንዚን ላይ እሳት ሲለኮሱ ተቀምጦ መመልከት የሚያስከትለው አደጋ እጅግ አደገኛ መሆኑን የማይገነዘብ ዜጋ ካለ ያንቀላፋ ዜጋ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ፣ አሁንም፣ ሌሎች ልዩነታችን እንደተጠበቁ ሆነው፣ ይህንን አገርና ህዝብ በመበተን ከፍተኛ ሚና ያለው ቅስቀሳ በጋራ ልንቋቋመውና፣ የተባለው 'ዘር የማጥፋትና የማፅዳት" ወንጀል ያልተፈፀመ ከሆነ፣ ወሬኞቹን በህግ ፊት በማቅረብ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸውና ሌሎች ተመሳሳይ ተንኮለኞችም ከዚሁ በቂ ትምህርት እንዲቀስሙ ማድረግ ተገቢ ብቻ ሳይሆን የዜጎች ግዴታም ነው፡፡

እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም፣ ይህ ድርጊት ያንድ ሰው፣ የምርጫው፣ ወይም ደግሞ ያንድ ሬዲዮ ጣቢያ ድርጊት ያለመሆኑ በጥንቃቄ ሊሰመርበት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ምርጫውና ሬዲዮ ጣቢያው ከተፍረከረከው ቅንጅት የኣንዱ ቡድንና ደጋፊዎቹ በሚያፈሱት ገንዘብ የሚንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ በተደራጀ ቡድን የሚሰራጭ የጥላቻ ፖለቲካ መሆኑን በጥንቃቄ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንን በአሃዝ ለማመልከት ይቻላል፡፡

በዊሺንግተን ከተማ ብዙ የተቃዋሚ ሬዲዮ ጣቢያዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ምርጫው ስንሻው ከሚያስተናግደው ሬዲዮ ውጪ ያሉት የተቃዋሚ ሬዲዮ ጣባያዎች በሳምንት ያንድ ሰዓት ፕሮገራም ለማስተላለፍ ያለባቸው የገንዘብ ችግር ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ሬዲዮኖቹን ስራችን ብለን የምንከታተል ሁሉ በሚገባ እናውቀዋለን፡፡ በሳምንት ያንድ ሰኣት ሬዲዮ ፕሮገራም ለማስተላለፍ የሚያስፈልገው ገንዘብ ከ 350 እስከ 500 ዶላር ይሆናል፡፡ በዚህ ሂሳብ በወር ከ 1,400 እሰከ 2,000 ዶላር ለማግኘት ሳይችሉ ቀርተው ዘግተው የሄዱ ሰዎች ኣሉ፡፡

በኣንፃሩ ደገሞ፣ በሰዓት 385 ዶላር የሚከፍለው "ኢትዮጵያዊነት" ሬዲዮ ከሰኞ አስከ ዓርብ ድረስ በየቀኑ የኣንድ ሰዓት ፕሮግራም ያስተላልፋል፡፡ ቅዳሜ ደግሞ የሶስት ሰዓታት፣ እሁድም የኣንድ ሰዓት ዝግጅት ኣለው፡፡ በድምሩ በሳምንት የዘጠኝ ሰዓታት፣ በወር የ 36 ሰዓታት የጥላቻ ፖለቲካውን ይረጫል፡፡ ስለዚህ፣ 36 ሰዓት በ 385 ሲባዛ የአንድ ወር ወጪ 13,860 (አስራ ሶስት ሺ ስምንት መቶ ስድሳ) ዶላር ይሆናል ማለት ነው፡፡ የዓመቱን ወጪ ብናሰላው ደግሞ 166,320 (ኣንድ መቶ ስድሳ ስድሰት ሺ ሶስት መቶ ሃያ) ዶላር መሆኑ ነው፡፡ የህ ከባድ ገንዘብ ነው፡፡

ይህንን ምን ያሳያል? የ'ኢትዮጵያዊነት" ሬዲዮ የሚያስተላልፈውና፣ በትግራይ ህዝብ ላይ በማተኮር የሚነዛው ደረቅ የፖለቲካ ጥላቻ፣ በተደራጀ ቡድን የሚመራና የጥላቻ ፖለቲካውን በደስታ የሚገዛ ከባድ ሃይል ከጀርባው መኖሩን ነው፡፡

እንገዲህ፣ ከላይ የጠቃቀስኳቸው ናሙናዎች በተደራጀ መልኩ የሚሰራጨውን ሲሆን፣ እስኪ በተናጠል የሚሰራጨውን የጥላቻ ፖለቲካ ደግሞ ምን እንደሚመስል እንቃኘው፡

**በትግራይ ህዝብ ላይ የተነዛ የጥላቻ-መርዝ**
**ናሙና ቁጥር** - 1

ከዚህ በታች የማቀርባቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለት የጥላቻ-ፖለቲካ ናሙናዎች ከሁን በፊት፣ ምርጫ-97 በተጠናቀቀ ማግስትና የቅንጅቱ መሪዎች ወደ ቃሊቲ ከመውረዳቸው በፊት፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ያገኙትን ወንበር ይዘው ፓርላማ ቢገቡ ለነሱና ለሃገር እንደሚጠቅም በማሳሰብ በበተንኩት ፅሑፍ ጠቅሻቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ያኔ የነበረኝ የምፒዩተር የግእዝ ፕሮግራም ችግር ስለነበረው ፁሑፉን በኢንተርኔት በስፋት ለማስነበብ አልቻልኩም ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ፣ ያኔ ሁሉም በስሜት ተወጥሮ ከራሱ ዘፈን በቀር ሌላ ነገር መስማት የሚፈልግበት ወቅት ስላልነበረ፣ ብዙ ሰዎች ፅሁፉን የተመለከቱት አልመሰለኝም፡፡ ስለዚህ፣ ያኔ በፅሑፌ ላይ የጠቀስኳቸው የጥላቻ ፖለቲካ ምሳሌዎች እዚሁ ደግሜ ማቅረቡ ለያዝነው ርእሰ-ነገር አስፈላጊ ጭብጥ ሆኖ አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ቀጥሎ የተመለከተው ፀረ-ትግራይ ህዝብ የሆነ ኣሳፋሪ የጥላቻ ፖለቲካ በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ኣማካኝነት የተሰራጨው ባሜሪካን ኣገር በሚኖርና ፕሮፌሰር ጥላሁን ይልማ በተባለ እውቅ ሳይንቲስትና የኣማራ ብሄር ተወላጅ ነው፡፡ መርዙን የረጨው February 1996 እና November 1996 ታትመው በወጡ "Ethiopian Review" በመባል በሚታወቀው ወርሓዊ መፅሄት ነው፡፡ ፅሁፉ የቀረበው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን፣ ኣንዲት ቃል ሳላዛንፍ እናዳለ ራሴ ወደ ኣማርኛ መልሸዋለሁ፡፡ (እጠቅሳለሁ)

**«በሰፊው የሚታመንበት ሃቅ ቢኖር፣ የትግራይና የኤርትራ ሰዎች ባለፉት ዘመናት ሌሎች ኢትዮጵያዊያኖች ለሰጧቸው ዕድልና ለዋሉላቸው ውለታ ምስጋና ቢስ መሆናቸውን ነው። ለብሄራዊ መሰረቴ ምንም ትርጉም ባልሰጠውም፣ እኔ ከኣራት ብሄሮች ማለትም ከኦሮሞ፣ ከጉራጌ፣ ከኣማራና ከትግራይ እወለዳለሁ። እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ኣንድም የኦሮሞ፣ ያማራና የጉራጌ ዘመዴ ወደ ትግራይ ወይም ወደ ኤርትራ ሄደው ሲኖሩ ኣላየሁም። የወንድ ኣያቴ ወልደኣብ ፈለማ ግን እንደሌሎቹ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ረሃብተኛና ልብስ ኣልባ ችጋራም የትግራይና የኤርትራ ስደተኞች ባዶ እጁ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ዱከም ሄዶ፣ ምናልባትም ከኦሮሞ ዘመዶቼ የተቀማ ይሆናል፣ ኣንድ ጋሻ መሬት ተሰጥቶት ይኖር ነበር። ደረቅና መካን ከሆነው የትውልድ መንደራቸው ለፈለሱት የትግራይና የኤርትራ ሰዎች፣ ትግርኛ ተናጋሪ ያልሆኑት ኢትዮጵያዊያኖች እጃቸውን ዘርግተው በመቀበል የመኖሪያ ቤት፣ የትምህርትና የስራ ዕድል እንዲሰጣቸው ኣድርገዋል። የትግራይና የኤርትራ ሰዎች የዩኒቨርሲቲውና የመንግስት ስራዎችን በመቆጣጠር፣ የተዋጣላቸው የንግድ ድርጅቶችን በመክፈት ብዙ ጊዜ ሌሎች ኢትዮጵያዊያኖች ስራ እናዳይቀጠሩና እድገት እንዳያገኙ በማድረግ ኣግልለዋል።**

**«እነሱ (የትግራይና የኤርትራ ህዝቦች) ኣስፈላጊ የሆነውን የሰውነት ክፍል በልቶ እንደሚገድለው ኣደገኛ ካንሰር ናቸው። ይህንን ካንሰር ቆርጠን ካልጣልነው በቀር ኢትዮጵ ያ እንደ ሃገር መቀጠሏ ያከትማል። ትግሮችና ኤርትራዊያኖች ባረቀቁት የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ተብየው መገንጠልና ሁሉም ብሄር/ብሄረሰቦች በየክልላቸው ተወስነው እንዲኖሩ የሚፈቅዱ ኣንቀፆችን ኣካቷል። ኣሁን እኛ መጠየቅ ያለብን እነሱ በራሳቸው ህገ መንግስት መሰረት የመጀምሪያዎቹ ተጠቃሚዎች በመሆን ወደ መጡበት ክልል እንዲባረሩና ኢትዮጵያም እንደ ሃገር ከትግርኛ ተናጋሪዎቹ የትግራይና የመረብ ምላሽ ህዝቦች መገንጠል ያለባት መሆኑን ነው።**

**«የተቀረው የኢትዮጵያ ግዛት ሳይበታተን እንደ ሃገር እንዲቀጥል ከተፈለገ፣ የትግራይና የኤርትራ ሰዎች ባጠቃላይ ከኢትዮጵያ መንጥረን መንቀል ይኖርብናል።**

**«በእርግጠኝነት ላረጋግጥላችሁ የምችለው ነገር ቢኖር፣ የትግራይና የኤርትራ ሰዎች በዚያ ደረቅ መሬታቸው ሰፍረው በህይወት መኖር የማይችሉ መሆናቸውን ነው። እጃቸውን ዘርግተው በመለመን የኢትዮጵያ ዜግነታቸውን ለመውሰድ ባስቸኳይ ተመልሰው ይመጣሉ። በተባረሩ ማግስት ወዲያውኑ ረሃብና መጥኔ ሲያቀምሳቸው፣ መዳብ ነው ብለው የወረወሩትን ወርቅ (ኢትዮጵያ) ፍለጋ በጉጉት ይመጣሉ።**

**«መርሳት የሌለብን ነገር፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከኤርትራና ከትግራይ ጋር ኣሁን ያለው ግኑኝነት ትርፉ ስቃይና ችጋር ብቻ መሆኑን ነው። ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚወርድ ቢኖር ድሆች፣ ስስታም ዘራፊዎችና ምስጋና ቢስ ስደተኞች እንጂ ሌላ ምንም ሃብትና እቃ የለም።**

**«ትግሮችና ኤርትራዊያኖች እንበለ ኢትዮጵያ ለህዝባቸው ምንም ምግብ እንደሌላቸው ለማሳመን ይህ ቅድሚያ ማግኘት ያለበት የመፍትሄ ሃሳብ ነው። ኢትዮጵያዊ ዜግነታችን ይመለስልን በማለት መጥተው ሲለምኑን በምን ሆኔታ እንደምንቀበላቸው ለመወሰን ሬፈረንደም መካሄድ ይኖርበታል።**

**«በግልፅ ለመናገር ያህል እንደነዚህ ያሉ የችጋር መንስኤ/ምንጭ የሆኑትን የኢትዮጵያ ህዝብ መልሶ ለመቀበል ፈቃደኛ የሚሆን ኣይመስለኝም። ይህ የሚያስታውሰን ቢኖር፣ «ልክ እንደ ሶሻሊዝም ከሌቦች ጋር መደራደር ኣያስፈልግም» የሚለው የድሮ የጉራጌ ፈሊጥ ነው። በኔ እምነት ኢትዮጵያ ለነዚህ ዜግነት መስጠት የለባትም ባይ ነኝ። ኣስተያየት ለመስጠት ያህል ግን፣ ምናልባት ኢትዮጵያ ክልላቸውን በሞግዚትነት እንድታስተዳድር ሊታሰብበት ይችላል።» (የጥቅሱ ትርጉም መጨረሻ)**

የሳይንቲስት ጥላሁን ይልማ ሙሉ ቃለ-መጠይቅ የእንግሊዝኛው ቅጅ ለማንበብ የሚፈልጉ እዚህ ድረ-ገፅ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ http://www.ethiopic.com/Tilahun4.htm

## በትግራይ ህዝብ ላይ የተነዛ የጥላቻ-መርዝ
## ናሙና ቁጥር - 2

ሌላው በጅምላ የትግራይ ህዝብን በመስደብ የተረጨው የጥላቻ-ፖለቲካ የተላለፈው ደገሞ ሆላንድ ኣገር በሚኖረውና ዶ/ር. ኣሰፋ ነጋሽ በተባለ የኣማራ ብሄር ተወላጅ ነው፡፡ ይቺን ቀንጨብ ኣድርጌ ለኣብነት የማቀርባት ጥቅስ “The Pillage of Ethiopia: by Eritreans and their Tigrean Surrogates” በሚል ኣሰፋ ከፃፈው መፅሃፍ የተወሰደ ነው፡፡ የመፅሃፉ ኣጠቃላይ ይዘት በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ-ፖለቲካ ነው፡፡ መፅሃፉ የተፃፈው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለሆነ የወሰድኩት ጥቅስ ኣጭር እንደመሆኑ መጠን፣ የንግሊዝኛውን እንዳለና ያንኑ ወደ ኣማርኛ በመመለስ ጭምር ነው፡፡ በዚህ ኣሳፋሪ መፅሃፍ ውስጥ በገፅ 86-87 ላይ “The Tigrean Sense of Justice Revisited” ከሚል ርእስ ስር እንዲህ የሚል ይነበባል፡፡ (እጠቅሳለሁ)

> **"For Tigreans, any issue in which a question of justice is involved, abstract considerations of what is just or unjust play a lesser role than that of the ethnic identities of the conflicting parties or persons engaged in the particular conflict. In short, in the Tigrean culture, the issue of injustice is not as important as the issue of the ethnic identities of the offender and the victim. In other words, the Tigrean sense of justice is a function of biological or ethno-linguistic relationship to the would-be offender and victim in a conflict. For the Tigrigna speaker, something is experienced as injustice when that injustice is perpetrated on a Tigrean by an outsider, depending on the relationship of this outsider to the would-be victim. For a Tigrean, any criminal offence that a Tigrean may commit against a non-Tigrean does not constitute an injustice as long as the one committing the offence is a Tigrigna speaker." (pp. 86-87)[2]**

> **«ለትግሮች፣ ማንኛውም ሁለት ወገኖችን የሚያካትት ኣንድ ቅራኔ ሲያጋጥማቸው፣ ጉዳዩን የሚያዩት ፍትሃዊ ነው ወይስ ፍትሓዊ ኣይደለም በሚል ሳይሆን፣ በቅራኔው የተካተቱት ሰዎች የዘር ሃረጋቸው ምንድን ነው ለሚለው የበለጠ ትኩረት በመስጠት ነው። ባጭሩ፣ በትግሮች ባህል፣ ቀዳሚ ቁምነገር ብለው የሚወስዱት የጉዳዩ ኢፍትሃዊነት ሳይሆን የተገላጋዮቹ ብሄራዊ ማንነት የበለጠ ትርጉም በመስጠት ነው። በሌላ ኣባባል፣ ትግሮች በፍትህ ላይ ያላቸው ኣመለካከት በበዳዩና በተበዳዩ መካከል ያለው የባዮሎጂ/የደም ትስስር፣ የብሄር ማንነትና የቋንቋ ምንነት መሰረት በማድረግ ነው። ለትግርኛ ተናጋሪዎች፣ ኣንድ ተግባር ኢፍትሃዊ ነው ተብሎ የሚወሰደው፣ ያ ኢፍትሃዊ ተግባር ኣንድ ትግሬ ያልሆነ ሰው በትግሬው ላይ የፈፀመው እንደሆነ ብቻ ነው። ላንድ ትግሬ፣ ኣንድ ሌላ ትግሬ በሌላ ኣንድ ትግሬ ያልሆነ ሰው የሚፈፅመው ወንጀል ኢፍትሃዊ ነው ተብሎ ኣይወስደውም። ኣንድ ወንጀል ኢፍትሃዊ የሚሆነው ወንጀሉ ትግሬ ያልሆነ ሰው በትግሬ ላይ ሲፈፅመው ብቻ ነው።»** (የጥቅሱ ትርጉም መጨረሻ።)

ሁለቱም የጥላቻ ፖለቲከኞች ያስተላለፉት መልእክት ግልፅ ስለሆነ የኔ ተጨማሪ ማብራሪያ ኣያስፈልገውም፡፡ እኔ ላሰምርበት የምፈልገው ነጥብ ቢኖር፣ ሁለቱም ሰዎች በፅሁፎቻቸው ላይ ኣንዲት ቃል እንኳ ገዢውን ፓርቲ ወይም ወያነን የማትኮንን መሆኑን ነው፡፡ ኩነኔው በሙሉ

---

[2] ("The Pillage of Ethiopia: by Eritreans and their Tigrean Surrogates" Adey Publishing Company, P.O. Box 361208, Los Angeles, California; Publisher: Dagnachew Teshome, Associate Publisher: Woobshet Tebicke, Production Manager: Tamerat Assfaw.)

የዘነበው፣ ኢህአዴግ ውቅያኖስ ተሻግሮ ዴንማርክ ድረስ በመምጣት በጦር ወንጀለኛነት የከሰሰኝ እኔው ምስኪኑን ጨምሮ፣ ባጠቃላይ በፈረደበት በትግራይ ህዝብ ላይ ነው፡፡

## በትግራይ ህዝብ ላይ የተነዛ የጥላቻ-መርዝ
## ናሙና ቁጥር - 3

የጥላቻ-ፖለቲካ፣ መጥፎ በሽታ ስለሆነ፣ በህይወት ያሉትን የትግራይ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ወደር የማይገኝለት ታሪክ ሰርተው ለተሰዉት የትግራይ ተወላጆች ጭምር ምህረት የለውም፡፡ ስለሆነም፣ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለማስከበር በታላቅ ጀግንነት ውድ ህይወታቸውን የሰዉት ንጉሰ-ነገስት፣ ኣፄ ዮሃንስ ኣራተኛን፣ ባዲስ የጥላቻ ሰይፍ ታሪካቸውን ይቆራርጣል፡፡ ሻለቃ ዳዊት ወልደ-ጊዮርጊስ የሚሉት የሸዋ ቅምጥል፣ ከሁለት ዓመታት በፊት (በጎርጎሳዊ ኣቆጣጠር 2006 ዓ.ም.) "ክህደት በደም መሬት" በሚል ስያሜ በፃፈው መፅሓፍ በገፅ 177 ኣፄ ምንሊክን ይክብ-ይክብና "የኣብየን ለእምየ" እንዲሉ የኣፄ ዮሃንስን ስም እንዲህ ሲል ያጎድፋል፡፡ (እጠቅሳለሁ)

**"እንዲያውም ኤርትራን ለጣልያን ያስረከቡት ኣፄ ዮሓንስ ናቸው፡፡ ኣፄ ምኒልክ የደረሱት የራስ ኣሉላ ሰራዊት ከባህር ጠረፍ ካፈገፈገ በሁዋላ ነው፡፡" (የጥቅሱ መጨረሻ)**

ወርቅ ነው፤ እንዲህ ያለን ድፍረት የሚሰጥ የጥላቻ-ፖለቲካም ኣለ! የዚህ መጣጥፍ ትኩረት ኣይደለም እንጂ፣ ስለ ራሱ ስለ ዳዊትም ሆነ ስለ መፅሓፉ በሰፊው ለመተቸት በወደድኩ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ኣገር በሚታመስበት ወቅት፣ እንደ ዳዊት ተመችቶኝ ጊዜ ኣልተረፈኝምና፣ እስካሁን ድረስ ብርታቱን የሰጠኝ ኣምላክ እድሜውን ከሰጠኝ ዳዊትንና መፅሃፉን ተመልሸ የምቃኛቸው እሆን ይሆናል፡፡

እንግዲህ፣ በተደራጀ መልኩና በተናጠል የሚሰራጨውን ኣውዳሚና ቢታኝ የጥላቻ-ፖለቲካ በተመለከተ፣ ከላይ የጠቃቀስኩት ለጊዜው የሚበቃ ይመስለኛል፡፡ ባጠቃላይ ይህንን ኣደገኛና ኣገር-በታኝ ፖለቲካ በተመለከተ ያሉኝ ጭብጦች ግን እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ በዚህ ወሳኝ ጉዳይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሰፊው እንደምቀጥልበት ጠቁሜ ለማለፍ እወዳለሁ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ይህንን ወቅታዊ መጣጥፌን ከመቋጨቴ በፊት፣ ከያዝኩት ጭብጥ ጋር በተያያዘ፣ ሁለት ነገሮችን ባጭሩ ለማከል እወዳለሁ፡፡ ከላይ በትክክል ለማስጨበጥ እንደሞከርኩት፣ የጥላቻ ፖለቲከኞች ዘመቻቸውን እያራመዱት ያሉት በዋናነት በትግራይ ህዝብ ላይ ነው፡፡ ሆኖም ዘረኞቹ በዚህ ብቻ ኣልተወሰኑም፡፡ የትግራይ ተወላጅ ያልሆነን፣ ነገር ግን፣ የትግራይ ህዝብ የማይጠላና ከትግራይ ተወላጅ ጋር የተጋባ/የተጋባች ጭምር በጠላትነት ፈርጀው እንደሚወጉዋቸው ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

ለኣብነት ያህል፤ በቅርቡ የቀድሞ የቅንጅት ም/ሊቀ-መንበር፣ ያሁኑ የኣንድነት ፓርቲ ሊቀ-መንበር፣ የሆነችው ውድ እህታችን ወ/ት. ብርቱካን ሚዲቅሳ የትግል ጓደኞቿን መርታ በሰሜን ኣሜሪካ ሰፊ የስራ ጉብኝት ማካሄዷ የሚታወስ ነው፡፡ በዚህ የስራ ጉብኝቷ ወ/ት. ብርቱካን ለኣገርዋ፣ ለፓርቲዋና ለደጋፊዎቿ ካበረከተቻቸው መልካም ስራዎቿ ኣንዱ በሚኖሶታ ያደረገችው ትህትና የተመላበት ንግግሯ በእጅጉ ጠቃሚና ሊበረታታታ የሚገባ ታላቅና ገንቢ እርምጃ ነው፡፡ ውድ እህታችን፣ ስም ባትጠራም፣ በድርጅቷ ስም በተደራጀው ድረ-ገፅ ኣማካኝነት፣ ኣዛውንቱ ዶ/ር. ጌታቸው ሃይሌ እንኳ ሳይቀሩ፣ ፅንፈኞች ሲነዙት የከረሙትን የጥላቻ-ፖለቲካ ኮንና፣ በድርጅቷ ስም የተሰደበውን የትግራይ ህዝብ ይቅርታ መጠየቋ ቆራጥነትን የሚጠይቅ ትልቅ ጀግንነት ነው፡፡ ኣገራችን ያበቀለቻቸው የጥላቻ-ፖለቲከኞች በነገሱባት ኣሜሪካ ሆኖ በመድረክ ላይ ወጥቶ "የትግራይ ህዝብ ኣልጠላም" ማለት፣ ይባስ ብሎ ደግሞ በድርጅቷ ስም ለተፈፀመው ኣፍራሽ በደል ይቅርታ መጠየቅ በእጅጉ ብልህነት፣ ለኣገር ተቆርቋሪነትና ቆራጥነት የሚጠይቅ እርምጃ ነው፡፡ በዚህ ኣጋጣሚ

ለወ/ት. ብርትኳን ሚድቅሳና ፈለግዋን ለሚከተሉ ሁሉ አክብሮት የተመላው ምስጋናየን ለማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡ እግዚአብሄርም ይባርካቸው፡፡

በወ/ት. ብርቱካን ቆራጥ እርምጃ ላይ፣ የሃይሉ ሻውል ዘበኛ በሆነው በምርጫው ስንሻውና "ኢትዮጵያዊነት" ብሎ በሚጠራው የጥላቻ-ፖለቲካ ልሳኑ፣ የዘነበው ስድብና ውርጅብኝ ሬዲዮኑን የሚያዳምጡ ሁሉ ስለሚያውቁት ብዙ መናገር አያስፈልገኝም፡፡ ምርጫው ስንሻው በተለይ በውድ እህታችን ላይ ሲሰነዝራቸው የነበሩ ስም የማጥፋት ተራ ስድቦችና የቅፅል ስሞች እዚህ መድገም ምርጫው ከሰጠመበት ማጥ ገብቶ አብሮ መዝቀጥ ስለሚሆን፣ በድፍኑ ድረጊቱን ኮንኘ ማለፍ እመርጣለሁ፡፡

ሌላው፣ ከጥቂት ሳምንታት በፊት፣ ባንዳንድ የጥላቻ-ፖለቲከኞች የፓል-ቶክ የኢንተርኔት የውይይት መድረኮችና በሌሎች የዜና ማሰራጫዎች አማካኝነት፣ መዓት እርግማንና ለጆሮ የሚቀፉ ተራ ስድቦች በሰቀቀን ያዳመጥነው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ-ማርያምን የሚመለከት ነው፡፡ እውቁ ምሁርና አዛውንት አባት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ-ማርያም፣ በዋሺንግተን ዲ.ሲ. በተጠራ ህዝባዊ ስብሰባ ከሰጡት ሰፊ መግለጫ፣ የጥላቻን አደገኛነት አስመልክተው የተናገሩት፣ ብልህነትና ቆራጥነትን የሚጠይቅ መልእክታቸው፣ በጥላቻ-ፖለቲከኞቹ አልተወደደላቸውም፡፡ የጥላቻ ፖለቲከኞችን ጭንቅላት አዙሮ ወደ ዕብደት የለወጠው የፕሮፌሰር መስፍን ወርቅ የሆነ ንግግር፣ ከኦዲዩ ወደ ወረቀት ስለገለበጥኩት፣ እስኪ እንመልከተው! (እጠቅሳለሁ)

> "ጥላቻ ቂምና በቀል ከማሰብ አይመነጨም፡፡ ከአእምሮ አይመነጨም፡፡ የእንስሳ ደመነብስ ውላጆች ናቸው፡፡ መንፈስን ከማርከስ፣ አእምሮን ከማወላገድ፣ ተጠያቂነት በሌለበት ሆኔታ ህይወትና ንብረትን ከማጥፋት በቀር ጥቅምንም ሆነ ክብርን አያመጡም፡፡ እስራኤልና ፍልጥኤም ምስክሮች ናቸው - ለዚህ፡፡ እንስሳ መሆን ቀላል ነው፡፡ የሚከብደው ሰው መሆን ነው፡፡ ዳዊት፣ 'ሰብ እሰብእ ዘክቡር ውእቱ ወየአእመረ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ ወተመሰለሙ' ይላል፡፡ (ሰው ክቡር መሆኑን ባለማወቁ አእምሮ እንደሌላቸው እንስሳት ሆነ፤ መሰላቸውም፡፡) ይህንን በደምብ እያየነው ነው፡፡ ጥላቻ ቂምና በቀል አእምሮን ያጨልማሉ፡፡ ክፋትን ዓላማ ያደርጋሉ፡፡ መረን በለቀቀ የግል ስልጣን ምኞት ከተመረዘ ሰው በቀር፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ባለስልጣን ለማድረግ የተቀየሰውን የትግል ዓላማ ወደ ክፋት ሊለውጥ የሚሞክር የለም፡፡
>
> "ከዚሁ የክፋት ዓላማ ጋር የተያያዘ ሌላ አደገኛና ከፖለቲካ አስተሳሰብ ውጭ የሆነ የስሜት ውላጅ አለ፡፡ ወያኔን ጠላት ብሎ በመሰየም ይጀምርና፣ መግቢያና መውጪያ የሌለው ጥቅጥቅ የስሜት ውዥንብር ውስጥ ይገባል፡፡ ወያኔ ለኤርትራ ተወላጆች መሸሻ አገር ሰጥቶ ባእድ በማድረግ ጀመረና፣ ጠላት አደረጋቸው፡፡ የወያኔ ፖለቲካ ተቃዋሚዎች ደግሞ፣ ወያኔን ጠላት ሲሉት አገር ሳይሰጡት ነው፡፡ የፖለቲካ ተፎካካሪዎች ጠላቶች ሊባባሉ አይገባም፡፡ ምንም ያህል ሰፊ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቢኖረንም፣ አንዱ የሌላውን ኢትዮጵያዊነት መገፈፍ አይችልም፡፡" (የጥቅሱ መጨረሻ)

እስኪ ልብ እንበል! ይህን የመሰለ ያንድ ታላቅ ምሁርና አስተማሪ፣ በረጅም እድሜ ባለፀጋነቱ ከፍተኛ የህይወት ተመክሮና ጥበብ የተላበሰ ሰው ተግሳፅና ምክር፣ ጭንቅላቱ በትክክል የማይሰራ፣ በጥላቻ የታወረ፣ የወደቀና የዘቀጠ ፍጥረት ካልሆነ በቀር፣ ማን ምን ክፉ ነገር ሊያወጣለት ይችላል? የኒህ ታላቅ ዜጋ አጭር ምክር የያዘው ጥልቅ ምስጢር ጊዜ ኖሮኝ በዝርዝር ለማስረዳት በወደድሁ ነበር፡፡ አጭር አስተያየት ለመሰንዘር ያህል ግን፣ ከፍተኛ ምስጢር ያዘለው የፕሮፌሰር መስፍን መልእክት፣ በከፍተኛ ውጥረት የምትገኘዋን አገራችን በመታደግ ትልቅ አስተዋፅኦ ያለውና ሊወደስ ሊቀደስ የሚገባው ታላቅ ምክር መሆኑን መግለፅ እወዳለሁ፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን፣ ሁሌም ቢሆን፣ ላመኑበት ሃሳብ በግልፅ መንፈስና በማሻያማ ቋንቋ መፃፍና መናገር ዋና መታወቂያቸው መሆኑን ስለማውቅ፣ ለኔ አዲስ ነገር ባይሆንም፣ ምክራቸው በጣም አስፈንድቆኛል፡፡ ስለሆነም፣ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሜ፣ ለሳቸው ካሁን በፊት የነበረኝና አሁንም ያለኝን ከፍ ያለ አክብሮት የተመላበት አድናቆቴን ልገልፅላቸው እወዳለሁ፡፡ እግዚአብሄር ይባርክዎ ኩቡር ፕሮፌሰር!

ሌላ በዚህ ኣጋጣሚ፣ በሊቀመንበሯ በወ/ት ብርቱካን ሚዲቅሳ ኣማካኝነት ለሁሉም የፓርቲዋ ኣባላትና ደጋፊዎች የማስተላልፈው ኣጭር መልእክት ኣለኝ፡፡

ኣገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ጥንቃቄ በሚያስፈልገው ወቅት ላይ እንደምትገኝ ለባለጉዳዩ መንገር ወይም ቀባሪን ማርዳት ይሆንብኛል፡፡ ባሁኑ ጊዜ፣ መልካም ኣጋጠሚ ያገኙ የመሰላቸው የሩቅና የቅርብ ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላቶች ኣሰፍስፈው እየጠበቁ እንደሆነ ከማንም የተሰወረ ኣይደለም፡፡ እድሜ ለኢህኣዴግ ኣመራር፣ በቅርቡ ኣገር የሆነችው ኤርትራ በራሷ የምትሆነው ነገር ባይኖርም፣ ከኣባይ ወንዝና ከቀይ ባህር ባሻገር ያሉና ከውሃችን ጋር ጉዳይ ያላቸው ሃይሎች፣ ኤርትራን እንደ መሸጋገሪያ ኮሪዶር ተጠቅመው ከሆነላቸው እኛን ለማተራመስ የማይፈነቅሉት ድንጋይና የማይምሱት ጉድጓድ እንደሌለ አትስቱትም፡፡ ስለዚህ፣ የያዛችሁት የሰላም ትግል ኣድካሚና እልህ ኣስጨራሽ መሆኑን ብረዳም፣ ኣሁን ኢትዮጵያ በምትገኝበት ሆኔታ ግን ከሱ የተሻለ ሌላ ምርጫ ያለ ኣይመስለኝም፡፡ ከዚህ በፊት ሌላ ምርጫ ለመውሰድ የሚቻልበት፣ እኔ ራሴ የምደግፈው፣ ብዙ ዕድል ነበር፡፡ የተቃዋሚው ጎራ በጥላቻ-ፖለቲከኞች የተበከለ በመሆኑ ግን ዕድሉ ከሽፏል ብቻ ሳይሆን ተመልሶ ሊመጣም ኣይችልም፡፡ በኢትዮ-ኤርትራ ግጭት ማግስት፣ ኣገራችን ዘላቂ ጥቅምና ሰላም የምታገኝበት መልካም ኣጋጣሚ ተገኝቶ ሳለ፣ "የትግራይ ህዝብና የኤርትራ ህዝብ እየተባላ ካልኖረ በቀር የኛ ፀሓይ አትወጣም" ብለው የሚያምኑ እኩዮች ኣምክነዉታል፡፡ ስለሆነም፣ የፈለገውን ጊዜና ጉልበት ቢወስድ፣ ኣሁን እንደያዛችሁት፣ በስራ ላይ ያለውን ህግ ተከትሎ የሰላሙን ትግል መቀጠል ትልቅ ብልህነት መሆኑንና ሌላ ኣማራጭ እንደሌለም ልጠቁማችሁ እወዳለሁ፡፡

የፈለገው ጊዜ ቢወስድ ወሸት እውነትን ማሸነፍ ኣይቻለውም፡፡ በቅርብና በጥልቅ የማውቀው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጎራ በማያሻማ መንገድ ምርቱና ግርዱ ተለይቶ ነጥሮ ወጥቷል፡፡ የሰላሙን ትግል በግላጭ፣ የብረቱን ትግል ደግሞ በድብቅ፣ በኤርትራ በኩል፣ ለማስኬድ ሲያሴር የነበረው ሁሉ በማያዳግም ሆኔታ ተጋልጦ እርቃኑ ወጥቷል፡፡ "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ፣ ኣብረህ ተወቀጥ" ሆነና፣ እናንተም ለረጅም ጊዜ ከማን ጋር እየሰራችሁ እንደሆነ ሳታውቁ፣ በቅንነት ኣብራችሁ በመጓዝ መሰቃየታችሁ ኣሳዛኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ስቃያችሁ ግን፣ ከይሲዎቹ ተመንጥረው እንዲወጡ ዕድል በመክፈት፣ ለኣገራችን ከፍተኛ ጥቅም ማስገኘታችሁ የሚካድ ኣይደለም፡፡ ይህንን የምልበት ምክንያት በዝርዝር በቅርቡ ኣቀርባለሁ፡፡ ስለዚህ፣ ምንም እንኳ በቅንጅት ውስጥ የነበረው ምርትና ግርድ ነጥሮ የተለየ ቢሆንም፣ ኣሁንም ቢሆን መሰሪ የጥላቻ-ፖለቲከኞች በውሰጣችሁ ሰርገው በመግባት ፓርቲያችሁን እንዳያምሱ ከባድ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይንን ኣጋጣሚ ተጠቅሜ በትህትና ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፡፡ በስራዎቻችሁም ሁሉ መልካሙን እመኛለሁ፡፡

ኣጋጣሚውን ተጠቅሜ ኣጭር መልእክቴን ካስተላለፍኩ ዘንዳ፣ ወደተነሳሁበት ርእሰ-ነገር ተመልሸ መጣጣፌን ለመቋጨት እሞክራለሁ፡፡

እዚህ ላይ ምንም ሳልደብቅ ግልፅ ማድረግ የምፈልገው ኣብይ ጉዳይ ኣለ፡፡ ይኸውም ባሁኑ ጊዜ በትግራይ ህዝብ ላይ እየተነዛ ያለው የጥላቻ ፖለቲካ በዳያስፖራ ክልል ብቻ ተውጦ የሚቀር ወሬ ሳይሆን በየቀኑ ከትግራይ ህዝብ ጆሮ የሚደርስ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህወሓት እንዲያደርግልን የምንጠብቀው ጉዳይ ኣይደለም፡፡ ህዝባችንና ቤተሰቦቻችን ራሳቸውን ነቅተው እንዲጠብቁና ለማንኛውም ጥሪ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ የህወሓት ኣመራር ፈቃድና ድጋፍ ኣያስፈልገንም፡፡ ስለዚህ፣ የትግራይ ህዝብ በሱ ላይ የሚነዛውን ቅስቀሳ በተለያዩ ዘዴዎች እየሰማ፣ እየተገረመና እየተቆጨ መሆኑን መግለፅ እወዳለሁ፡፡ ለምሳሌ፣ ይቺው መጣጥፍ ገና ገበያ ሳትወጣ ትግራይ ትደርሳለች፡፡ የዚች መጣጥፍ ኣንድ ቅጅ ትግራይ መሬት ስትረግጥ ደግሞ ባንድ ቀን ብቻ በስፋት እንደምትዳረስ መገመት ኣያቅትም፡፡ በዚህ ገዢው ፓረቲም፣ እኛን ይውደደን ይጥላን በማያስጨንቅ፣ የስርጭቱ ተባባሪና ተጠቃሚ እንደሚሆን የሚጠራጠር ያለ ኣይመስለኝም፡፡

የቅጩን ለመናገር ያህል፣ ኣሁን ከሚሸረበው ሴራና ከሚነዘው ጥላቻ በመነሳት፣ ኢትዮጵያ ተከባብሮ መኖር የማይቻልባትና፣ የሞተላት ቀርቶ - የገደላት የሚኮፈስባት ኣገር ከሆነች፣ ለኔ ኢትዮጵያ የምትባል ኣገር ባፍንጫየ ትውጣ እላለሁ፡፡ "ካንሰር ነህ" የምባልባት ኣገር ዜጋ ከመሆን

ይልቅ፣ ካሁን በፊት ስቃወመው የነበረው የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 ተጠቅሜ ከኢትዮጵያ መገንጠልን እመርጣለሁ፡፡ ባሁኑ ጊዜ የኔ ሰሜት ይህ ነው፡፡ ይህ ስሜት የስንት የትግራይ ተወላጅ ስሜት እነደሆነ ለመረዳት፣ አጥኚ ካለ አጥንቶ ሊደርስበት ይችላል፡፡ አንቀፅ 39 ለጌጥ የተቀመጠ አንቀፅ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ካለ ደግሞ ራሱን የሚያታልል፣ ካለፈ ታሪክና ማስጠንቀቂያ ያልተማረ፣ የዋህ ሰው ብቻ መሆን አለበት፡፡

ስለዚህ፣ በዚህ አሳሳቢ ወቅት በትክክል ሊሰመርበትና ሊሰራበት የሚገባ አብይ ጉዳይ ካለ፣ ይህንን በትግራይ ህዝብ ላይ እየዘነበ ያለ ዘግናኝና የኢትዮጵያን ህልውና የሚፈታተን የጥላቻ ዘመቻ ባስቸኳይ እንዲገታ ማድረግ የሁሉም ተቆርቋሪ ዜጋ ግዴታ መሆኑን አፅንኦት ሰጥቸ ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ከላይ ያቀረብኳቸው መረጃዎች ለብዙ ሰው፣ በተለይም ፖለቲካ ለሚከታተሉ ሰዎች፣ አዲስ ግኝት አይመስሉኝም፡፡ ይሁን እንጂ ከኛ ከትግራይ ተወላጆች ድምፅ በቀር የሌሎች ኢትዮጵያዊያን ድምፅ፣ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ዓይነቱ፣ ጎልቶ የወጣ የለም ማለት ይቻላል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍንም ለመልካም አቋማቸው ያተረፉት ያው የጥላቻውን ጠበል አብረውን መጠጣት ነው፡፡ አንዳንድ ብልጣ-ብልጦች "በመካከላችን የትግራይ ሰዎችም አሉ" ለማለት ያህል ብቻ ተቆርቋሪ መስለው ለመቅረብ ሲሞክሩ እታዘባለሁ፡፡ ይህ ራስን ለመጥቀም የሚደረግ የማስመሰል ተግባር ግን ከጠባብ የዳያስፖራ ክልል ወጥቶ ትግራይ ደርሶ ለውጥ የማምጣት ሃይል የለውም፡፡ ይቺው አጭር መጣጥፍ፣ የምርጫው ስንሻውን አስደንጋጭ ዲስኩር ይዛ፣ በዛሬው ቀን የትግራይ መሬት ስታጥለቀልቅ ግን ከፍተኛ ድምፅ እንደምታሰማ መጠርጠር አይቻልም፡፡ የሚሰራ ስራ ካለ ይህንን እኔ ትግራይ መሬት እያደረስኩት ያለው መረጃ የሚቀለብስና የሚያሽር መሆን ይኖርበታል፡፡

በመጣጥፌ መዝጊያ መድገም የምፈልገው፣ አሁን ከቁጥጥር ውጪ የሄደውና በትግራይ ህዝብ ላይ እየዘነበ ያለው አገር በታኝ መርዝ ለመግታት የሚቻለው፣ አንዳንድ ኢጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ጥቂት ቃላት በመወርወር ብቻ አይደለም፡፡ ጉዳዩ አገር ሊበትን የሚችል መሆኑን በሚገባ ተሰምሮበት፣ ወጥ የሆኑና ድምፃቸው ጎልቶ የሚሰማ የተቃውሞ አቋም መግለጫዎች እስከ ማውጣት ድረስ የሚሄድ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል፡፡ ይህንን እያልኩ ያለሁት የትግራይ ተወላጅ በመሆኔ ብቻ ያለመሆኑን በቅንነት ማስረገጥ እፈልጋለሁ፡፡ ይህ መልእክቴ የማስፈራሪያ ወይም የማጋነን ጉዳይ ሳይሆን፣ ግልፅ ሆኘ ለመናገር፣ በጥላቻው-ፖለቲካ አራማጆች ላይ ግልፅ አቋም ተወስዶ የማያወላዳ ማስታገሻ ካልተበጀለት በቀር፣ እየዋለ ባደረ ቁጥር፣ አንድ ሆኔታ የተፈጠረ ለታ፣ ኢትዮጵያን ከናካቴው የመበተን ሚናው እጅግ የጎላ መሆኑን ለማስታወስ ስል ነው፡፡

**እግዚአብሄር/አላህ ኢትዮጵያን ይጠብቅ!**
**ዘረኞችና የጥላቻ ፖለቲከኞች ይታረሙ ወይም ይገለሉ!**